# የዜግነት ውትድርና በኢትዮጲያ፤ የተጠባባቂ ኃይል፣ የብሔራዊ ውትድርና እና የሚሊሻ ስርዓቶች ዳሰሳ[1]

**ኮሎኔል ተሾመ ገብረማሪያም ደስታ[2] እና ዶ/ር ቃለአብ ታደሰ ሥጋቱ[3]**

## *አሕጽሮት*

*በሙያው ከሰለጠነ መደበኛ ሠራዊት በተጨማሪ የዜግነት ወታደሮችን መጠቀሚያ የሆኑ ሦስት ስርዓቶች  ተጠባባቂ ኃይል፣ ብሔራዊ ውትድርና እና የሚሊሻ ሥርዓት ናቸው። የዚህ ጸሁፍ ዓላማም በኢትዮጲያ በአግባቡ የተደራጀ የዘመናዊ ጦር ስርዓት ከተጀመረበት  ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ስላሉት ሦስቱ የዜግነት ውትድርና ስርዓቶች ታሪክ፣ የህግ ማዕቀፍ እና አጭር ትንተና ለማቅረብ ያለመ ነው። ጥናቱ በተጠቀሱት የዜግነት የውትድርና ስርዓቶች ላይ የተጻፉ መጽሐፍትና የሌሎች አገሮች ተሞክሮዎች፣ በነጋሪት ጋዜጣ የታወጁ አዋጆችን በመመርመርና ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ወታደራዊ ግዳጆችን ከተወጡና ከመሩ ወታደራዊ መኮንኖች ጋር ቃለመጠይቅ በማድረግ የተጠና ሲሆን፤ ጥናቱ በኢትዮጲያ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓት "ብሔራዊ ጦር" በሚል መጠሪያ የተጠባባቂ ኃይል ለመጀመሪያ ጊዜ በሕግ እንደተቋቋመ፣ ይህም ይብዛም ይነስም ዓላማውን ያሳካ እንደነበር፣ ነገር ግን ንጉሡ "የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት" ለመጀመር ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ እንደቀረና፤ ወታደራዊው መንግሥት (ደርግ) የሶማሊያን ወረራ ለመመከት ሚሊሻዎችን በማሰባሰብ፣ ወጣቶችን ለብሔራዊ ወታደራዊ አገልግሎት በከፍተኛ ሁኔታ በመመልመልና የተጠባባቂ ኃይልን ሥርዓት በመዘርጋት የተራዘመ የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ እንደቆየ እና የኢሕአዴግ መንግሥትም ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ በ1995 ዓ.ም የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል የተቋቋመ ሲሆን፤ ከአገራዊ ሪፎርም በኋላም በ2015 ዓ.ም ከነበረው የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል በተጨማሪ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የብሔራዊ ውትድርና እንደታወጀ ይገልጻል። ጥናቱ በአገራችን በወታደራዊ ጥናት መስክ በዜግነት ውትድርና ላይ የተጠኑ ጥናቶች ጥቂት በመሆናቸው በዘርፉ ያለውን የእውቀት ክፍተት ለመሙላትና ያለመ ሲሆን፤ አሁን ያለውን የዜግነት ውትድርና ጠንካራ ለማድረግ ያለፉትን ስርዓቶች ድክመትና ስኬቶችን መገምገም አስፈላጊ መሆኑን በመጠቆም ይደመድማል።*

**ቁልፍ ቃላት፡** ኢትዮጲያ፣ የዜግነት ውትድርና፣ ተጠባባቂ ኃይል፣ ብሔራዊ የውትድርና አገልግሎት፣ ሚሊሻ፣ መከላከያ ሠራዊት

## 1 መግቢያ

በኢትዮጲያ ታሪክ አገርን ከጠላት የመከላከል ጉዳይ በማንኛውም ዜጋ በተለይም በገበሬው ትከሻ ላይ የወደቀ ሆኖ በአዋጅ ክተት በተባለ ጊዜ እየዘመተ ጠላትን አባርሮ ወደ ቀድሞው ኑሮው ይመለስ እንደነበር የረጅም ዘመን ታሪካችን ይናገራል።[4] "በሰላም ጊዜ አራሽና ቀዳሽ በችግር ጊዜ አልሞ ተኳሽ" የሚለው ብሂል የዜግነት ወታደር የተለመደ አሰራር እንደነበር የሚያሳይ ነው። የውጭ ወራሪዎችና የውስጥ ሥጋቶች ሲከሰቱ ዜጎች በጊዜያዊነት የአካባቢያቸውን ማኅበረሰብና አገራቸውን ለመጠበቅ ራሳቸውን የማስታጠቅና የማደራጀት የዜግነት ኃላፊነትና የሞራል ግዴታ አለባቸው የሚለውም ባህል የዜግነት ውትድርና ጽንሰ ሐሳብ መሠረት ነው።[5] በብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት በመሳተፍ፣ የተጠባባቂ ኃይል አባል በመሆን አልያም የሚሊሻ አገልግልሎት በመሥጠት የዜግነት ውትድርና ውስጥ የሚሳተፍ ሰው በሕይወቱ ሁለት  ሃላፊነት ይወስዳል። በአንድ ወገን በሲቪል ማህበረሰብ ውስጥ ሰራተኛ ሲሆን በሌላ ወገን ደሞ በጦር ኃይሎች ውስጥ አገልግሎት ይሰጣል። በመሆኑም ለዚህ ይመስላል የቀድሞው

---

[1] ጸሐፊዎቹ ጥናቱን ለማከናወን ድጋፍ ያደረጉትን የኢፌዲሪ የመከላከያ ዋር ኮሌጅን፣ በመከላከያ ሚኒስቴር የተጠባባቂ ኃይል ማደራጃና ማስተባበሪያ ቢሮን እና የቀድሞ ሰራዊት ቬተራንስ ማህበርን ያመሰግናሉ።

[2] በመከላከያ ዋር ኮሌጅ መምህር እና የሕብረት ዘመቻ ዲፓርትመንት ሃላፊ፤ destateshome209@gmail.com

[3] የመከላከያ ዋር ኮሌጅ በዓለም አቀፍና የአካባቢ ደህንነት ዲፓርትመንት ተመራማሪ፤ kaleab.sigatu@gmail.com

[4] ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927 1983" 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት፡፡ ገጽ 524፡፡

[5] Samuel P. Huntington: The Soldier and the State: the Theory and Politics Civil-Military Relations. Cambridge: The Belknap Press of Harvard University Press, 1967. እና Phil Klay: The Citizen-Soldier: Moral Risk and the Modern Military. Washington, DC, the Brookings Institution, 2016.

የዩናይትድ ኪንግደም ጠ/ሚኒስቴር ዊንስተን ቸርችል "ተጠባባቂ መሆን ሁለት ጊዜ ዜጋ መሆን ነው።" ያለው።[6]

በታሪክ ውስጥ የወታደራዊ የሰው ኃይል ፍላጎትን ማሟላት መንግስታትን ሲፈታተን የቆየና የማህበረሰብን የአኗኗር ሥርዓት የቀየረ ሁኔታ የፈጠረ ነው።[7] ፕሮፌሽናል የሙሉ ጊዜ ወታደሮች መፈጠር ወይም ውትድርና ቋሚ የሆነ ሙያ እየሆነ መምጣቱ የተቀሩትን ዜጎች የአገር መከላከል የውትድርና ሸክምን አቃሎላቸዋል፤ በሌሎች ሥራዎች ላይ ብቻ እንዲያተኩሩም አድርጓል። ነገር ግን በዘመናችን የሀገር መከላከል ጉዳይ በቋሚ ወታደሮች ላይ ብቻ የተጣለ ኃላፊነት ሳይሆን በተደራጁ የዜጋ ውትድርና አገልግሎት ሰጪዎችን አስፈላጊ ሲሆን ከወታደሩ ጋር ለግዳጅ የሚሰለፉትን የተጠባባቂ ኃይል፣ ብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት እና የሚሊሻ ስርዓቶችን ያጠቃለለ ነው።[8] ሌ/ኮሎኔል አበበ ወልደትንሳይ የዜግነት ውትድርናን አስፈላጊነት እንደሚከተለው አስቀምጠውታል፤

> ምንም እንኳን የአንድ ሀገር ወታደር ዋና ተግባሩ የአገርን ሠላም መጠበቅና ደህንነቷን ማረጋገጥ ቢሆንም፤ሠራዊት በተፈጥሮው አምራች ኃይል ያልሆነ በአገር ኢኮኖሚ ግንባታ ውስጥ በቀጥታ ተሳትፎ የሌለው፣ ሌላው ያመረተውን የሚመገብ፣ የአንድን አገር ኢኮኖሚ የሚፈታተን ኃይል በመሆኑ በስልጣኔ የገፉት አገሮች ይህንን ኃይል በእጅጉ በመቀነስ የዜግነት ውትድርና አገልግሎት ማድረግ አስፈላጊነቱን አምነው በተግባር ላይ ማዋል ከጀመሩ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ተቆጥሯል።[9]

በመሆኑም ከቋሚ ፕሮፌሽናል ወታደሮች በተጨማሪ ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች በውትድርና ሞያ ወይም የአገርን ሉአላዊነትና ሠላም ለማሥጠበቅ ከዋናው ሥራቸው በተጨማሪ መሳተፋቸው አነስተኛ ቋሚ ወታደር እንዲኖር በማድረግ በዛ ያሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች በዜግነት ውትድርና መሳተፋቸው የኢኮኖሚ ጥቅም የሚያስገኝ ነው።

## 1.1 የተጠባባቂ ጦር ሥርዓት

ወታደራዊ የተጠባበቂያ ኃይል ማለት በቋሚነት ሲቪል ሙያተኛ የሆነና ወታደራዊ ስልጠናን ወስዶ ወደ ሲቪል ሙያው ተመልሶ እየሰራ የሚገኝ ነገር ግን ወታደራዊ ጥሪ ሲደረግለት ከሰራዊቱ ጋር በመሆን አልያም ብቻውን ወታደራዊ ግዳጅን የሚያከናውን የሲቪል ዜጋ-ወታደር የሆነ ወታደራዊ ተቋም ነው። በዋናነትም በሠላም ጊዜ የአገርን ወታደራዊ ወጪ በመቀነስ ነገር ግን ወታደራዊ አቅምን ጠብቆ ለመቆየት የሚያስችል ሥርዓትም ነው። በብዙ አገሮችም እንደ ሁለተኛው የመከላከያ መስመር ሆኖ ለመሥራትም የተነደፈ ነው። በተጨማሪም የአንድ አገር ተጠባባቂ ኃይል ማለት የሀገሪቱ የመከላከያ ኃይል አንደኛው አካል በመሆን በዋናነት የሰላምና የደህንነት ቀውሶች በሚኖሩበት ወቅት ብቻ ግዳጃቸውን የሚወጡ ቀጣይነት ያለው የሙሉ ጊዜ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ የሌለባቸው ወታደሮችን የሚያመላክት ነው።[10]

የተጠባባቂ ኃይል እንደየአገራቱ ሥርዓት የሚለያይ ሲሆን አንዳንድ አገሮች ተጠባባቂን የሚጠቀሙት ለወታደራዊ አገር መከለከል ግዳጅ ብቻ ሲሆን፤ ሌሎች ደግሞ በአገር ውስጥ በሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች ጊዜ ነው፤አንዳንድ አገራት ደግሞ ከአገር ውጭ በሚደረጉ እንደ ሠላም ማስከበር ላሉ ዘመቻዎች ጭምር ይጠቀሙባቸዋል።[11]

---

[6] Currie, James T. and Richard B. Crossland. "Twice the Citizen: A History of the United States Army Reserve, 1908-1983." Army Reserve, Washington, DC, 1984. Page xiv.

[7] Lars Mjoset – Stephen Van Holde (eds.): The Comparative Study of Conscription in the Armed Forces. New Jersey, JAI Press Inc., 2002.

[8] Jukka Mattila et al.: Meanings of Military Ranks, Defence Studies, 17:4 (2017) 359-378.

[9] ሌ/ኮሎኔል አበበ ወልደትንሳይ፤ "ቀ.ሠ ና ጦ. ሠ" (ቀዳማቂ ኃይለ ሥላሴ እና ጦር ሠራዊት)፣ አዲስ አበባ፤ 2000 ዓ.ም፡፡ ገጽ 266

[10] NRFC "What is the National Reserve Forces Committee?" https://www.act.nato.int/opportunities/national-reserve-forces-committee-nrfc/ Accessed on 21 May 2022.

[11] Ujházy, László. The Role of Reservists and Reserve Associations today. Security and Defence Quarterly 2018; 19(2)

ሁሉንም የውትድርና ሥራዎች መተካት ባይችሉም ተጠባባቂዎች የተወሰኑትን ዋና ዋና የውትድርና ተግባራት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ማሳካት ይችላሉ። ለምሳሌ በአሜሪካ የተጠባባቂ ኃይል ለሠራዊቱ ከሚወጣው በጀት 6% ብቻ በመጠቀም፣ 20%ቱን የሰራዊቱ ጠቅላላ ኃይል መሸፈን ይችላል። በዩናይትድ ኪንግደም እኤአ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ለማንኛውም ግዳጅ ከሚሰማራው ኃይል ውስጥ 10% የሚሆነው ተጠባባቂ ኃይል ሲሆን እኤአ ከ2003 ዓ.ም 25,000 የሚሆኑ የተጠባባቂ ኃይል አባላት በአብዛኛው በኢራቅ እና አፍጋኒስታን ግዳጅ ላይ ተሰማርተው ነበር፤ አውስትራሊያ በሰለሞን ደሴቶች ውስጥ ያላትን ወታደራዊ ኃይል ለማቆየት የተጠባባቂ ኃይሎችን በማሰማራት ለመደበኛ ሠራዊት ከምታወጣው በአራት እጥፍ ርካሽ በሆነ ወጪ ለማቆየት ችላለች።[12] ለዚህም ነው ብዙ የምእራብ አገራት ሁልጊዜም ቢሆን የተጠባባቂ ኃይል የሚኖራቸው።

በአሁኑ ጊዜ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ወደ 206,000 የሚጠጉ "ተዋጊ ዜጎች" ወይም የተጠባባቂ ኃይል አባላት ያሉት፤ ይህ ማለት ከጠቅላላ ሠራዊቱ 19% የሚሆኑት ናቸው። ከነርሱም ውስጥ ወደ 90% የሚጠጉ የሲቪል ጉዳዮች ሰራተኞች፣ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የህክምና እና የጦር ካምፖችና የጦር ሰፈሮች አስተዳዳሪዎች፣ ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሚሆኑት ደግሞ የመጓጓዣ ሥራዎችን፣ እና አንድ አራተኛ የሚሆኑት የስለላ እና ወታደራዊ ፖሊስ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። በካናዳ ከጠቅላላው ሠራዊት ውስጥ ግማሽ ያህሉ ተጠባባቂዎችን ኃይል ያቀፈ ነው። በአውስትራሊያ ውስጥ ከጠቅላላው ኃይል 43% የሚሆኑት ተጠባባቂዎች ናቸው፤ በፈረንሣይ በአመት በአማካይ ወደ 23 ቀናት የሚያገለግሉ ወደ 60,000 የሚጠጉ ተጠባባቂዎች አሉ።[13]

በብዙ የተጠባባቂ ኃይልን የሚጠቀሙ አገሮች እንደተለመደው ከፍ ያለ ቁጥር ያላቸው ተጠባባቂዎች እንደ ህክምና፣ ምህንድስና፣ ሎጂስቲክስ፣ ህግ፣ የውጭ ቋንቋዎች፣ የህዝብ ግንኙነት፣ የመረጃ አያያዝ ስርዓቶች፣ አስተዳደር እና ልማት የመሳሰሉ ልዩ ችሎታዎች ያሏቸው ሲሆን፤ ለሰላም ማስከበርና ለመልሶ ግምባታ ግዳጆች የተጠባባቂ ኃይልን ይጠቀማሉ። በተመሳሳይ የውትድርና አገልግሎት ለተጠባባቂ ኃይሉ አባል እና አሰሪዎቻቸው ከፍተኛ ጥቅሞን ይሰጣል። በውትድርና አገልግሎት ላይ እያለ ለጠባባቂው የሚሰጠው የአመራርና የተለያዩ የትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራሞች፣ የተጠባባቂውን የግል እውቀትና ስብዕና ብቻ ሳይሆን ለተቀጠረበት ተቋምና ለአካባቢው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

የተጠባባቂ ኃይል አባላት በተለምዶ በአመት ውስጥ የተወሰነ ጊዜ ስልጠና የመውሰድና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሲሆን በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በበጎ ፈቃደኝነት የሙሉ ጊዜ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ። ተጠባባቂዎች የቀድሞ መደበኛ ሠራዊት አባል ወይም የተጠባባቂ ኃይል አዲስ ገቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

በአጠቃላይ ስንመለከተው የተጠባባቂ ኃይል የሚከተሉት አራት የግዳጅ ባህሪያት አሉት፤[14] 1ኛ በመደበኛ ኃይሎች ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወይም በበቂ ጥንካሬ የማይኖሩ የልዩ ባለሙያ ችሎታዎችን መስጠት ያስችላል። እነዚህ በተለምዶ የሕክምና፣ የኮምፒውተር፣ የምህንድስና እና ሌሎች ስፔሻሊስቶች ናቸው። 2ኛ አጋዥ አቅምን መስጠት የሚችል ነው። ይህ ማለት በአንዳንድ ተልእኮዎች ውስጥ ሙሉ ወታደራዊ ብቃቶች የማይፈለግባቸውን ግዳጆች መወጣትን ያመለከታል። ይህም የበለጠ ከፍተኛ የሰለጠኑ እና ከፍተኛ ዝግጁነት ያላቸው መደበኛ ኃይሎች ለበለጠ ተፈላጊ ለሆኑ ግዳጆች ብቻ ለማዋል ነጻነትን ይሠጣል። 3ኛ ተጨማሪ አቅምን መስጠት ያስችላል። ይህ ማለት በመደበኛ ኃይሎች የሚከናወኑ ተግባራት በተመለከተ ሲሆን፤ መደበኛውን ሰራዊት በግዳጅ ወቅት ለመተካት ወይም ለማጠናከር የሚያስችል አቅምን ይፈጥራል። 4ኛ ሠራዊትን በፍጥነት የማሳደግና የማብዛት አቅምን ይፈጥራል።

[12] Guillaume Lasconjarias "Send the Reserve! New Ways to Support NATO through Reserve Forces Contents" Research Paper. Research Division – NATO Defense College, Rome – No. 99 – November 2013. https://www.files.ethz.ch/isn/175315/rp_99.pdf Accesse on 21 May 2022.

[13] Guillaume Lasconjarias "Send the Reserve! New Ways to Support NATO through Reserve Forces Contents" Research Paper. Research Division – NATO Defense College, Rome – No. 99 – November 2013. https://www.files.ethz.ch/isn/175315/rp_99.pdf Accesse on 21 May 2022.

[14] National Reserve Forces Committee (NRFC). NATO's ACT. https://www.act.nato.int/nrfc Accessed on 30 May 2022.

ይህ ማለት ድንገተኛ የጸጥታና የደህንነት አደጋ ሲከሰት፤ መጠነ ሰፊ የመከላከያ ሰራዊትን ለማንቀሳቀስ የማስፋፊያ መሰረት ነው። ለብዙ ዘመናት የነበረውና የተለመደው የተጠባባቂ ጦር ሚናም ይህ ነበር።

በተጨማሪም የተጠባባቂ ኃይል አባላት ብዙውን ጊዜ በአንድ አገር ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው ስለሚኖሩ መደበኛ የመከላከያ ኃይል በሌለባቸው የአገሪቱ ክፍሎች ውስጥ እንደ ብሔራዊ መከላከያ ሠራዊት ተወካይና ፊት ሆነው ያገለግላሉ። በማኀበረሰቡ ውስጥ ስለሚኖሩና ስለሚሠሩም በመከላከያ ሠራዊቱ እና በማኀበረሰቡ መካከል እንደ የባህል ድልድይ ወይም መገናኛ ሆነው ያገለግላሉ።

## 1.2 ብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት (Conscription) ሥርዓት

"አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጲያ አንድነት" በሚል ርዕስ በተክለ ጻዲቅ መኩርያ በተዘጋጀው መጽሐፍ፤ በ1888 ዓ.ም መስከረም ወር ላይ፣ ንጉሠ ነገሥት ሚኒሊክ የጣሊያንን ወረራ በቅርብ አረጋግጠው፣ ለአድዋ ጦርነት የክተት አዋጅ በይፋ ነጋሪት ያወጁት የሚከተለውን መልዕክት በማስተላለፍ ነበር፤

> "እግዚአብሄር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ፤ እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ። ከእንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉም ነውና ስለእኔ ሞት አላዝንም። ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም፤ ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም። አሁንም አገር የሚያጠፋ፤ ሃይማኖትን የሚለውጥ፣ በፊት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባህር አልፎ መጥቷል። እኔም የአገሬን ከብት ማለቅ፤ የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር። አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። የአገሬ ሰው ከአሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም። አንተም እስካሁን አላስቀየምኸኝም። ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለሃይማኖትህ ስትል በሃዘንህ እርዳኝ። ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ። አልምርህም። ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም..."[15] ብለዋል።

ይህ የንጉሠ ነገሥቱ ጥሪ ግዴታን የሚያሳይ ብሎም ማስጠንቀቂያምንም የያዘ የዘመቻ ጥሪ የሚባል ሲሆን ሀገር በተወረረበት ወቅት ሁሉም በሚችለው አቅሙ እንዲዘምት አልያም ድጋፍ እንዲያደርግ የሚጠይቅ ነበር። በአብዛኛው የ20ኛው ክፍለ ዘመን ወታደራዊ ምልመላ የብሔራዊ ውትድርና አስተምህሮዎች ዋነኛ ገጽታ ነበር። በዓለማቸን ታሪክም ሁለቱም የዓለም ጦርነቶች የተካሄዱት የግዳጅ ብሔርዊ ውትድርና አገልግሎት በሚሰጡ ወታደሮች ነው። እ.ኤ.አ. በ1949 የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ቃልኪዳን ድርጅት (ኔቶ) መስራች ከነበሩት 12 ሀገራት መካከል ካናዳ ብቻ በግዳጅ ብሔርዊ ውትድርና አገልግሎት ላይ የተመሰረተ የውትድርና ሥርዓት የሌላት ሲሆን አይስላንድ ደግሞ ጭራሹኑ ወታደር አልነበራትም። ዩናይትድ ኪንግደም፣ ሉክሰምበርግ እና ዩናይትድ ስቴትስ በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የወታደሮች ምልመላ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት መተግበር ጀምረው ነበር። የግዳጅ ብሔርዊ ውትድርና አገልግሎት ምልመላ እስከ 1990ዎቹ አጋማሽ ድረስ በምእራባውያን አገሮች ውስጥ ዋነኛው የሰላም ጊዜ ምልመላ ዘዴ ነበር። ልክ እንደዚሁ የምስራቁ በዋርሶ ስምምነት በነበረበት ጊዜ ሁሉ (1955-91) ሁሉም አባላቱ የግዳጅ ብሔርዊ ውትድርና አገልግሎት ተጠቅመዋል።

አንዳንድ ጥናቶችም እንደሚያሳዩት የሀገሪቱ ሕዝብ ለመከላከያ ሠራዊት ያለው ድጋፍ የሚጨምረው ወታደሮች በብሔራዊ ውትድርና የተመለመሉ ሲሆን እንደሚሆን ያሳያል። በ34 የአውሮፓ አገሮች ላይ ከእ.ኤ.አ ከ1997 እስከ 2012 ድረስ በተደረገው ጥናት በብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ያላቸው አገሮች ለወታደሩ የሚሰጡት ሕዝባዊ ድጋፍ ከፈተኛ መሆኑን ያሳያል።[16] ጥናቱም አገሮች ምን አይነተ የወታደር ምልመላ ያስፈልጋቸዋል ለሚለውን በወታደራዊ ሳይንስ ውስጥ ላለ ምሁራዊ ክርክር ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው ነው።

ለምሳሌ በኤርትራ "ብሔራዊ አገልግሎት" ማለት የብሔራዊ አገልግሎት እና በተጠባባቂ ኃይል ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት ነው። እ.ኤ.አ. በ1998 በኢትዮጲያና ኤርትራ ጦርነት ምክንያት በታወጀውና ያልተነሳውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት በማድረግ በ1995 በወጣው የብሄራዊ አገልግሎት አዋጅ አንቀጽ 21(1) ላይ

---

[15] ተክለ ጻደቅ መኩሪያ፤ "አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጲያ አንድነት" አዲስ አበባ፤ ገፅ 226፡፡

[16] Choulis, I., Bakaki, Z., & Böhmelt, T. Public Support for the Armed Forces: The Role of Conscription. Defence and Peace Economics, 1–12. (2019). doi:10.1080/10242694.2019.1709031

እንደተደነገገው የብሔራዊ አገልግሎት ጊዜ እስካሁን ድረስ ላልተወሰነ ጊዜ ተራዝሟል።[17] በዲያስፖራ የሚኖሩ ኤርትራዊያን ስደተኞች እንደሚሉት ከሀገር ለመሸሽ ዋና ምክንያታቸው የግዜ ወሰን የሌለው የብሔራዊ አገልግሎት ግዳጅ ነው።[18]

የሚከተሉት ነጥቦች የ1995 የብሔራዊ አገልግሎት አዋጅ ላይ የተጠቀሱ ናቸው።[19] የብሔራዊ አገልግሎት ከ18 እስከ 40 ዓመት የሆኑ ሁሉም ኤርትራዊ ዜጎች ብሔራዊ አገልግሎት የመሳተፍ ግዴታ አለባቸው። ብሄራዊ አገልግሎት ለ6 ወር በስልጠና ማእከል ውስጥ ወታደራዊ ስልጠናን መውሰድ እና ለ12 ወር ወታደራዊ አገልግሎት ወይም የልማት ስራዎች መስጠትን ያመለክታል። የተጠባባቂ ወታደራዊ አገልግሎት ማለት በክተት ጥሪ ወቅት አገልግሎት ለመስጠት ግዴታ ያለባቸው የብሔራዊ አገልግሎት ሰጥተው ያጠናቀቁና በተጠባባቂ ጦር ውስጥ የማገልገል ግዴታ ያለበት ዜጋ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጠው አገልግሎት ነው። በተጠባባቂ ጦር ውስጥ የማገልገል ግዴታ ሁሉም ግለሰብ 50 ዓመት እስኪሞላው ድረስ ሲሆን እነሱም ሀ) ብሄራዊ አገልግሎታቸውን ያጠናቀቁ ዜጎች፣ ለ) በትጥቅ ትግል ውስጥ ያገለገሉ እና በአሁኑ ጊዜ ሰላማዊ ህይወትን እየመሩ ያሉ ታጋዮችን እና ሚሊሻዎች ፣ ሐ) በአሁኑ ጊዜ በሕዝብ፣ በግል እና በመንግሥት ዘርፎች ውስጥ የሚሰሩ የቀድሞ ተዋጊዎች፣ እና መ) በጦር ኃይሎች እና በፖሊስ ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩ ዜጎች ናቸው። በብሔራዊ አገልግሎት የመሳተፍ ግዴታ ያለበት ዜጋ ወደ ውጭ አገር እንዲሄድ ይፈቀድለታል። ነገር ግን ይህ ሊሆን የሚችለው 1) ብሔራዊ አገልግሎት እንዳጠናቀቀ ወይም ከብሔራዊ አገልግሎት ነፃ መሆን ሲችል እና 2) የብሔራዊ አገልግሎት ምዝገባ ካርድ ያለው ዜጋ ደግሞ 60,000 ብር በማስያዝ ወደ ውጭ አገር እንዲጓዝ ሊፈቀድለት እንደሚችል ሕጉ ያስቀምጣል።

እስራኤል በምትከተለው አስገዳጅ የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ውስጥ ከ18 አመት በላይ የሆናቸው እያንዳንዱ እስራኤላዊ ዜጋ አይሁዳዊ፣ ድሩዝ ወይም ሰርካሲያን በእስራኤል መከላከያ ሰራዊት ውስጥ እንዲያገለግሉ ይጠይቃሉ። ሌሎች እስራኤላውያን አረቦች፣ ሀይማኖታዊ ሴቶች፣ ያገቡ ግለሰቦች እና በህክምናም ሆነ በአእምሮ ብቁ አይደሉም የተባሉት ግን ከግዳጅ ወታደራዊ አገልግሎት ነፃ ናቸው። ከወታደራዊ አገልግሎት ነፃ የሆኑትም ቢሆኑ ብዙዎቹ በእስራኤል መከላከያ ሠራዊት ውስጥ በፈቃደኝነት ያገለግላሉ። ወደ ወታደራዊ አገልግሎት የገቡት ወንዶች ቢያንስ ለ32 ወራት እንዲያገለግሉ እና ሴቶች ቢያንስ ለ24 ወራት እንዲያገለግሉ ይጠበቃሉ።[20]

የመከላከያ አገልግሎት ህግ 5747 - 1986፤ የውትድርና አገልግሎት በእስራኤል እና በውጭ አገር ለሚገኙ የእስራኤል መንግስት ዜጎች ሁሉ ይሠራል። ምንም እንኳን ሌላ ዜግነት ቢኖራቸውም፣ በቋሚነት በውጭ አገር የሚኖሩ ቢሆኑም፣ የእስራኤል ዜጋ ባይሆኑም በእስራኤል ቋሚ ነዋሪዎች ላይም ይሠራል። የግዴታ አገልግሎት ግዴታ ለማገልገል ብቁ የሆነ ወንድ ሁሉ ከ18 እስከ 29 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናል።[21]

---

[17] European Asylum Support Office (EASO) "Country Of Origin Information Report - Eritrea: National Service, Exit, and Return." 2019. The State Secretariat for Migration, Switzerland. https://coi.euaa.europa.eu/administration/easo/PLib/2019_EASO_COI_Eritrea_National_service_exit_and_return.pdf. Accessed on 08 September 2022.

[18] HORN International Institute for Strategic Studies. Open-Ended Conscription in Eritrea's National Military Service: Here is How to Improve the Policy. HORN POLICY BRIEF. 23 September 16, 2019 https://horninstitute.org/wp-content/uploads/2019/09/OPEN-ENDED-CONSCRIPTION-IN-ERITREA%E2%80%99S-NATIONAL-MILITARY-SERVICE-.pdf. Accessed on 08 September 2022.

[19] Unofficial English Translation of the Gazette of Eritrean Laws, 1995-10-23, Vol. 5/1995, No. 11, Page 16. Eritrea - National Service Proclamation No. 82/1995. (ilo.org). https://www.ilo.org/dyn/natlex/natlex4.detail?p_lang=&p_isn=79562&p_country=ERI&p_count=24 Accessed on 08 September 2022.

[20] Our Soldiers | IDF | IDF (www.idf.il) https://www.idf.il/en/mini-sites/our-soldiers/ Accessed on 22 June 2022

[21] Israel Defense Service Law (1986) (jewishvirtuallibrary.org) https://www.jewishvirtuallibrary.org/israel-defense-service-law-1986 Accessed on 22 June 2022

በብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ከዓለም ቀዳሚ እንደሆነችና ረጅም ዘመን እድሜ ያለው ልምድ እንዳላት የምትጠቀሰው ቱርክ ናት፡፡ እንደ ባሕል ተቆጥሮ ይህን አገልግሎት ያልፈጸመ ዜጋ በሕብረተሰቡ ዘንድ ዝቅተኛ ግምት ይሰጠው ነበር፡፡[22] እ.ኤ.አ በ1982 የወጣው የቱርክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 72 ሁሉም ዜጋ ብሔራዊ አገልግሎት መስጠት እንዳለበት እንደሚከተለው ይደነግጋል፡፡ "ብሔራዊ አገልግሎት የማንኛውም ቱርክ መብትና ግዴታ ነው፡፡ ይህ አገልግሎት በጦር ኃይሎች ውስጥም ሆነ በሕዝብ አገልግሎት ውስጥ የሚከናወንበት ወይም እንደ ተፈጸመ የሚቆጠርበት መንገድ ሌላ ዝርዝር በህግ ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡"[23] በቱርክ ህግ የብሄራዊ አገልግሎት በወታደራዊ አገልግሎት ህግ (ህግ ቁጥር 1111) የተደነገገ ሲሆን፤[24] በተጨማሪም የተጠባባቂ መኮንኖች እና የተጠባባቂ ወታደራዊ አገግሎት ህግ (ህግ ቁጥር 1076) ተደንግጓል፡፡[25] በወታደራዊ አገልግሎት ሕግ ቁጥር 1111 አንቀፅ 1-3 መሰረትም ማንኛውም ወንድ የቱርክ ዜጋ በዚህ ህግ መሰረት የውትድርና አገልግሎቱን የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

## 1.3 የሚሊሻ ሥርአት

ሚሊሻ የሚለው ቃል በብዛት በአካዳሚክ በሥነ ጽሑፍ እና በዜና አውታሮች ውስጥ በሁለት መንገድ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡[26] በአንድ በኩል በአዎንታዊ መልኩ፣ ተግባራቸው ማህበረሰቡን፣ የፖለቲካ ስርዓቱን፣ የአገር ግዛትን እና ንብረትን መጠበቅ የሆነ ታጣቂ ዜጎችን፤ በሌላ በኩል በአሉታዊ መልኩ ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ የሆኑትን እንደ የጦር አበጋዞች ያሉ አሸባሪዎችን ወይም አማጺ ቡድኖችን ያመለክታል፡፡ በዚህ ጥናት የሚዳሠሰው የአካባቢ ሚሊሻ የአካባቢን ደህንነትና ጸጥታ ለማስፈን የራሳቸውን ድርሻ በመውሰድ የሀገር ውስጥ ሰላምን ለማስፈን ከሀገር መከላከያ ሠራዊትና ከሌሎች የደህንነትና የጸጥታ ኃይሎች ጎን በመሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱትን ኃይሎች ይሆናል፡፡

የሚሊሻ ኃይሎች በይበልጥ በአካባቢያቸው ከሚገኝ የፖሊስ ኃይል ጋር በመሆንና ተቀናጅቶ በመስራት ወንጀልና የሕዝቡን ሰላም የሚነሱ እንቅስቃሴዎችን ይከላከላሉ፡፡ የአካባቢ ሚሊሻ ኃይል በአካባቢው በሚገኝ የመከላከያ ሠራዊት ማሰልጠኛ ተቋም በመግባት አስፈላጊና ለተልዕኳቸው ተገቢ የሆነ አነስተኛ ስልጠና በመውሰድ ጸጥታን ለማስከበር በህብረተሰቡ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ናቸው፡፡[27] የአካባቢ ሚሊሻ ኃይሎች በማህበረሰቡ ውስጥ በመሆን በአካባቢያቸው በሚደረጉ ማንኛውም የልማት እንቅስቃሴዎች ከህብረተሰቡ ጎን በመሰለፍ አጠቃላይ ማህበራዊ ኑሯቸውን ይመራሉ፡፡ አስፈላጊ በሆኑ ከመኖሪያቸው ባልራቁ የአካባቢ ሰላምና ጸጥታ የማስከበር ስራዎች እና አደጋዎች ሲደርሱ ግዳጃቸውን ይፈጽማሉ፡፡ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ተቋምም እንደ አስፈላጊነቱ ተገቢውን ቁሳዊና ቴክኒካዊ እገዛዎች ያደርግላቸዋል፡፡

በተለምዶ በጥንት በሮማውያን ዘንድ ያለው ሚሊሻ ሥርዓት "የገበሬ ወታደርና" በመባል ይጠራ ነበር፡፡[28] በተመሳሳይ መልኩ በኢትዮጲያ ዘመናዊ ወታደራዊ ባህል የሚሊሻ ኃይል ባብዛኛው በገጠሪቱ የአገሪቱ ክፍል የሚገኝ የዜግነት ውትድርና ሥርዓት ተቋም ሲሆን በአከባቢ መስተዳድር እየተመራ የአካባቢ ፖሊስ ተግባርን ለመርዳትና ለማከነወን የሚውል ኃይል ነው፡፡ የሚሊሻ ስርዓት በጣም ግልፅ የሆነ ስልታዊ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን እሱም እጅግ

---

[22] ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927 1983" 2006 ዓ.ም፤ አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት፡፡ ገጽ 524፡፡

[23] Turkey's Constitution of 1982 with Amendments through 2017. https://www.constituteproject.org/constitution/Turkey_2017.pdf?lang=en Accessed on 22 August 2022

[24] Turkey: Law No. 1111 of 1927, Military Law , 20 March 1927, https://www.refworld.org/docid/3ae6b4d020.html Accessed 1 Septmber 2022

[25] Reserve Officers and Reserve Military Officers Law (No. 1076) » TR Laws (av-saimincekas.com) https://www.av-saimincekas.com/en/laws/1076-numbered-reserve-officers-and-substitute-military-officers-law/ Accessed 1 Septmber 2022

[26] George T. Kurian: The Encyclopedia of Political Science. Washington, DC, CQ Press, 2011.

[27] Britannica. Militia. Online: https://www.britannica.com/topic/militia

[28] William Duane: Military Dictionary. Philadelphia, W. Duane, 1810.

በጣም ብዙ የህዝብ ክፍልን ለማንቀሳቀስ ያስችላል፤ ይህም ከትላልቅ ወረራዎች በአገር ላይ ሲካሄዱ ከፍተኛ የሆነ ብሔራዊ መከላከያ ግዳጆችን መወጣት ያስችላል።[29]

## 2. በኢትዮጲያ ዘመናዊ ታሪክ የነበሩ መንግሥታት የተጠባባቂ ኃይል፣ የብሔራዊ አገልግሎት እና የሚሊሻ ስርዓቶች

በኢትዮጲያ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፊት በነበሩት ነገስታት እነደ ተጠባባቂ ኃይል የሚታየው አገሪቱ ጦርነት በገጠማት ጊዜ የሚጠራው ህዝብ ነበር። ለምሳሌ በአድዋ ጦርነት አፄ ምንሊክ ለህዝቡ የክተት ጥሪ ባቀረቡበት ጊዜ ህዝቡ ያለውን ትጥቅ ይዞ በከተተበት ጊዜ ህዝቡ እንደ ተጠባባቂ ነበር ማለት ይቻላል አልያም እንደ ብሔራዊ የግዳጅ አገልግሎት።[30] ሪቻርድ ፓንክረስት በመጽሐፋቸው በጥንታዊቷ ኢትዮጲያ ወታደራዊ አገልግሎት ከመሬት ይዞታ ስርዓት ጋር በቅርበት የተያያዘ ነበር። ጭሰኞች በጦርነትም ሆነ በድንገተኛ ጊዜ ለጌታቸው የውትድርና አግልግሎት እንደሚሰጡ በመረዳት ነበር የባላባቱ መሬት ላይ ሥራቸውን የሚሰሩት። በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸው ተዋጊዎች በሚያስደንቅ ፍጥነት ሊዘምቱም ይችላሉ። በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነበረው ጣሊያናዊ ተጓዥ ፍራንቸስኮ ሱሪያኖ ንጉሠ ነገሥቱ 'ከሁለትና ከሦስት መቶ ሺህ ባነሰ ሰው አይደልም የጦርነት ሜዳውን የያዘው' በማለት ሲጽፍ አልቫሬስ ደግሞ የኢትዮጲያ ነገሥታት ከፈለጉ በሁለት ቀናት ውስጥ 100,000 ሰዎች እንዲሰበሰቡ መጥራት ይችላሉ። ሲል ጽፏል። በማለት ይገልጻሉ።[31] በጥቅምት 15 ቀን 1900 ዓ.ም ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ በኢትዮጲያ ለመጀመሪያ ጊዜ በፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ የሚመራ የጦር ሚኒስቴር ቢያቋቁሙም[32] ከዛ በኋላ የተደረጉ ጦርነቶች በሙሉ ከመደበኛ ወታድር ውጪ ያሉትን ዜጎች በስፊት ያሳተፉ ነበሩ።

ገሥጥ ተጫኔ እንደሚሉት የንጉሡ እና የደርግ ስርዓት የነበሩት የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት አዋጆች ከአርፍተ ነገሮች ውስጥ "አብዮታዊት እናት አገር ..." ከሚሉ የተጨመሩ ቃላቶች ውጪ በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ተመሳሳዮች ናቸው። "የማንኛውም መንግሥት መቆሚያ አገርና ሕዝብ በመሆኑ።"[33]

> በሁለቱም አዋጆች የወጡት የመንግሥት አመራር ቀውስ በደረሰበትና የአገሪቱም ሠላም አስጊ ሁኔታ ላይ በወደቀበት ወቅት በመሆኑ ይበልጥ ያመሳስላቸዋል። በተለይ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅ የወጣበት ወቅት አገሪቱ በጦርነት በፖለቲካና በኤኮኖሚ ቀውስ የተወጠረችበት ነበር። ... በዚህ የተበላሸ "ከባቢ አየር" ምክንያት የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት አጀንዳ ሲነሳ ተገንጣዮቹ፣ የመንግሥት ተቃዋሚዎች፣ መንግሥት የሚያራምደውን ርዕዮተ ዓለም የጠሉ፣ ኢትዮጲያ ጠንክራ መቆሟን የማይፈቅዱ እንዲሁም በሌላው መስዋዕትነት መኖር የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተቃውሞ ፕሮፓጋንዳቸው በአዋጁ ላይ ስለዘመቱበት ጉዳዩ የማንኛውም ዜጋ ግዴታ መሆኑን በበጎ ገጽታው ወደ ሕዝቡ ለማስረፅ አዳገተ። ስለዚህ "ልጆቻችንን በጦርነት እሳት ለመማገድ ነው" በማለት የአጉረመረመው ሕዝብ የበዛ ነበር።[34]

### 2.1 ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የነበሩው የተጠባባቂ ኃይል ሥርዓትንና በሥራ ላይ ያልዋለው ብሔራዊ አገልግሎት

እንደተለመደው በቀድሞው ዘመን የኢትዩዮጲያ ነገሥታቶች የውጭ ጠላት ሲመጣባቸው ሕዝባቸውን ለማዘጋጀት "ክተት ሠራዊት" የሚል አዋጅ ያወጡ ነበር። እንደዚሁም ቀዳማዊ ኃይል ሥላሴ ኢትዮጲያን ለመውረር በኤርትራ እና በሱማሌ ግዛት በኩል ተደራጅቶ የመጣባቸውን የፋሽት ጦር ለመከላከል የክተት ሠራዊት አዋጅ መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም አወጡ። በዚያን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ይህን አዋጅ ያስነገሩት በየክፍለ ሀገሩና

---

[29] Meller, Bjern: "Conscription and its Alternatives" in Mjoset and Honde (Eds.) (2002.)

[30] ከብ/ጄነራል ውበቱ ፀጋዬ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፤ ግንቦት 26፤ አዲስ አበባ 2014 ዓ.ም፡፡

[31] Richard Pankhurst "The Ethiopians: A History." Blackwell Publishing, Oxford, 2001. Page 69.

[32] ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል "ዝክረ ነገር" 1962 ዓ.ም አዲስ አበባ፤ ገጽ 223፡፡

[33] ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927 1983" 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት፡፡ ገጽ 524፡፡

[34] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 525፡፡

በየአውራጃው የሚገኘውን የሕዝብ ሠራዊት ለማሰባሰብና ለማዘጋጀት ነው እንጂ በተሟላ የጦር ኃይል በተጠንቀቅ ከሚጠባበቀው የሙሲሊኒ ጦር ጋር ጦርነቱን ለመክፈት አልነበረም። በአውሮፓም አገሮች ሲሠራበት የቆየው ልማድ አንድ መንግሥት ከሌላው ጋር ሲጋጭና ጠቡ ወደ ውጊያ እንደሚያመራ ሲታይ በመጀመሪያ የሚወሰደው እርምጃ የአገሩን ጦር ለመሰብሰብና ለማዘጋጀት (Moblization Generale) መወሰኑን ማስታወቅ ሲሆን፤ ሁለተኛ ደግሞ ውጊያውን ለመጀመር ለባለጋራው የጦር መግለጫ (Declaration De Guerre) መስጠት ነው።[35] ንጉሠ ነገሥቱም በዚህ መሰረት የሚከተለውን አዋጅ አወጁ።

> የክተት አዋጅ፤ ሞአ አንበሳ ዘምነገደ ይሁዳ፤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጲያ። ያገሬ የኢትዮጲያ ሰው ኢትዮጲያ ከቀዳማዊ ምኒልክ ዠምሮ ሲያያዝ መምጣቱና በነጻነቱም ታውቆና ተከብሮ መኖሩን ታውቀዋለህ። ካሁን ቀደም ኢጣሊያ የዛሬ 40 ዓመት በብልኀቱና በጉልበቱ ተመክቶ የኢትዮጲያን ነጻነት አጥፍቶ ሕዝቡን እንደ ባሪያ አድርጎ ለመግዛት ተመኝቶ አገራችን መካከል መጥቶ ቢወጋን ግፍ የማይወደም አምላካችን ረድቶን ድል ማድረጉን ለኛ ቢሰጠን የሄደውን አገራችንን አልፈለግንም። በሐማሴንና በሱማሌም በኩል ወሰን እየገፋ ርስታችንን ወስዶ በዚያው በወሰደው አገር ላይ ያሉት ወንድሞቻችን የተሸከሙትን የባርነት ቀንበር ዐይንህ የሚያየው ዦሮህ የሚሰማው።
>
> እነሱ ላይ በሚሰራው ግፍ ስናዝን የሄደውን አገራችንን ሳንፈልግ አሁን ደግሞ በሞላው አገራችን በሚኖረው ሕዝብ ላይ የባርነት ቀንበር ለማሸከም አስቦ በውጋዴ በኩል በድብቅ ጦር አምጥቶ ጠብ ያልፈለጉትን የኛን ሰዎች ቢገድልብን የተዋዋልነውንም ውል ቢያፈርስብን ለዓለም ሰላም ተብሎ ወደ ቆመው የመንግሥታት ማኅበር እኛም ገብተናልና እንደ ሕጉ የወልወል ጠብ በሽማግሎች ታይቶ በደለኛው እንዲታወቅ ብለን ለመግሥታት ማኅበር አመለከትን።
>
> ነገሩም ገና በሽማግሎች ሳይታይና ሳይፈረድ ኢጣሊያ ጦሩን በትግሬና በውጋዴ ወሰን ስላቀረበ እንደ ገና ለመንግሥታት ማኅበር ብናመለክት ማኅበሩ ነገሩ በሽማግሎች ይታይ ብሎ ፈረደልን። . . . ይህም ሁሉ ሲሆን ኢጣሊያ ወደ ወሰናችን በየጊዜው ጦር እያመጣ መጨመሩን አልተወም። እኛም በሽማግሌ ታይቶ በሰላም ይፈጸም የምንለውን ሁሉ ኢጣሊያ ከመለማመጥ ቆጥሮት ከ3 ሺሕ ዘመን ይበልጥ በነጻነት የኖረችውን በጥንታዊትነቷ የታወቀችውን ሽማግሌዋን አገራችንን ነጻነቷን አጥፍቼ እውስዳለሁ በማለት ስለተመኘ ለመጠቃት በመታሰባችን እጅግ አዝኛለሁና ያገሬ የኢትዮጲያ ሰው ጉልበት ያለህ በጉልበትህ ጉልበት የሌለህ በሐዘንህ ርዳኝ። በጉልበትም በሐዘንም የምትረዳበት ምክንያቱ ለኃይማኖትህና ለነጻነትህ እንደ አባትና እንደ ልጅ እየተሳሰበ ሲረዳዳ ለኖረው ለንጉሠ ነገሥትህ ኮርቶ ነጻነቱን ለሚያሳየው ባንዲራህ ስትል ነው። . . .[36]

ይህ መግቢያው ሲሆን 11 የሚሆኑ መመሪያዎችም ነበሩት። ከዚህ ጥናት ጋር የተያያዙት 1ኛ፣ 4ኛ፣ 5ኛ፣ 11ኛው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

> 1ኛ በሳል በጉንፋን የምትሞተውን ሞት ከሩቅ አገር እኛን ለማጥቃት ለመጣ ጠላታችን ባገርህና በርስትህ በቤትህ ላይ ሆነህ መመከት አቅቶህ ላገርህ ለኢትዮጲያ ሞት ብትነፍጋት ደምህንም ሳይፈስ ብትቀር በፈጣሪህ የምትወቀስበት በዘርህ የምትረገምበት ነውና የተለመደ የዦግንነት ልብህን ሳታበርድ ወደ ፊት የሚቆይህን ታሪክህን እያሰብህ ጠንክረህ ለመዋጋት ቆርጠህ ተነሳ። 4ኛ ባላባትም የሆንክ ሁሉ ለዘመቻ የደረሱትን ለጆችህን ይዘህ ላገር ጥበቃ አላፊ የሚሆን እንደራሴህን ላገረገዢው  እንደራሴ እየሰጠህ ካገረ ገዢህ ጋራ እንድትነሳ። በሽምግልና ዘመቻ የማትችል ግን አንተ አገር ጠብቅ፣ ልጆችህ ካገረ ገዥው ጋራ ይነሱ። 5ኛ የሹማምንትና የወታደርም ልጅ ለዘመቻ የደረስህ ከዚህ ቀደም ከደንብ ያልገባህና ለጌታ ያላደርክ ባገር ውስጥ ሥራ ሳትይዝ የተቀመጥክ ጠመንዣ ያለህ ጥይትና ሥንቅህን ጠመንዣ የሌለህ ጠመንዣና ጥይት ሥንቅህንም ዳርጌሃለሁና አገረ ገዥህን ተከትልህ እንድትዘምት።

[35] ዘውዴ ረታ “የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት፡ 1ኛ መጽሐፍ 1923 እስከ 1948 ዓ.ም” አዲስ አበባ፡ ሻማ ቡክስ፣ 2005 ዓ.ም ገጽ 166፡፡

[36] ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል “ዝክረ ነገር” 1962 ዓ.ም አዲስ አበባ፤ ገጽ 276–279፡፡

> 11ኛ የዘመቻ አዋጅ ከተነገረ በኋላ የወንበዴነት ሥራ ስትሠራ ለጠላት ሥንቅም ነገርም ስታቀብል የተገኘህ ርስትህንና ገንዘብህን ትወረሳለህ። ያለምሕረትም በሞት ፍርድ ትቀጣለህ። [37]

ከላይ ከቀረበው አዋጅ የተደራጀ የተጠባባቂ ኃይል፣ ሚሊሻ ወይም ታጣቂ ባለመኖሩ ምክንያት ነጉሠ ነገሥቱ የክተት ጥሪውን ያስተላለፉት ለሁሉም ዜጋ ነበር።

### 2.1.1 የንጉሠ ነገሥቱ ብሔራዊ ጦር

በጥቅምት 24 ቀን 1948 ዓ.ም የተደነገገው ሁለተኛው የተሻሻለው ሕገ መንግሥት አዋጅ አንቀጽ 29 እንደሚለው

> *"ንጉሠ ነገሥቱ ፓርላሜንት እየተስማማበት ጦርነት ለማወጅ መብት አለው። ለሰላም ጊዜና ለጦርነት ጊዜ የሚያስፈልገውን የጦር ኃይል ይወስናል። ለጦር ኀይል ጠቅላይ አዛዥ ስለ ሆነ የጦሩን ኃይል ያደራጃል፤ ያዛል። ለጦር መኮንኖች ማዕረግ ይሰጣል። የጦር መኮንኖችን ማዕረግ ያሳድጋል፣ ያዛውራል፣ ወይም ያሰናብታል። እንዲሁም የጦር ጊዜ አስተዳደርን፣ የጦር ሕግን ወይም አገር የሚጠቀምበትን አስቸኳዩን ነገር ያወጃል። በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት መከላከያ ወይም በግዛቱ አንድነት ላይ አደጋ የሚያመጣውን ነገር ለማስወገድና መከላከያውንም አንድነቱንም ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ያደርጋል።"* [38]

በዚህም መሰረት የንጉሠ ነገሥቱ ብሔራዊ ጦር መቋቋም 1951 ዓ.ም ትእዛዝ ቁጥር 21[39] (ጥቅምት 21 ቀን 1921 ዓ.ም በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የጽሕፈት ሚኒስትር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ስም) የወጣ ሲሆን፤ ትእዛዙ በጦርነት ጊዜ ለንጉሠ ነገሥት መንግሥት መከላከያ እንደዚሁም በሰላም ጊዜ ላገር ውስጥ ጸጥታ ማስከበሪያ የሚሆን ተጨማሪ ኃይል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ መሆኑን የሚገልጽ ነበር። ገስጥ ተጫኔም "የጦር ሠራዊቱንና የፖሊሱን ኃይል መቆጠብ ሲያስፈልግ ተደራሽነት በሌላቸው አካባቢዎች ፀጥታን የሚያስከብር፣ አገሪቱ አጠቃላይ ጦርነት ውስጥ ብትገባ ተጠባባቂ ጦር ሆኖ የሚሰራ ኃይል በቀላል ወጪ ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመጠናቱ ነው።" በማለት ይገልጹታል።[40] አያይዘውም ሌላውን ፖለቲካዊ ምክንያት እንደሚከተለው ሲያስቀምጡ፤

> የምድር ጦር ሠራዊት አቋም እንደገና እየሰፋ፣ አገሪቷም ራሷን ከአጥቂዎች የመከላከል አቅሟ እየጎለበተ ቢሄድም ከመደበኛ ግዳጁ ወጣ ያሉ የውስጥ ሠላምን የሚመለከቱ ጥቃቅን ክስተቶችን ለማምከን ጦር ሠራዊቱን ማሳተፍ ተመጣጣኝ ኃይል ካለመሆኑም በተጨማሪ ድንበር የማስከበር ተግባሩን የሚያዳክም በፍጥነት የመንቀሳቀስ ችሎታውንም አናሳ፣ በፖሊስ ኃይልም በኩል ከሰው ኃይል ከአደረጃጀትና ከንቅናቄ አኳያ የሚታይ የአቅም ውስንነት ከመኖሩም ሌላ በአስተዳደር ችግር ምክንያት ማጉረምረም ጀምሮ ነበር። አለቆቹ ማጉረምረሙን ሰምተው ለችግሩ ተገቢውን መፍትሄ ከመሻት ይልቅ በቁጣና በማስጠንቀቂያ ለማፈን በመጣራቸው ውስጥ ውስጡን እየተትመከመከ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያመልክቱ ፍንጮች ታዩ። ይህ ሁናቴ መንግሥትን አማራጭ ኃይል ወደ ማውጠንጠን መራው። ነገሩ እዚህ ላይ እንደደረሰ በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች ይታዩ የነበሩ የጎሳና የኃይማኖት ግጭቶች በመንግሥት አስተዳደር ላይ ተቃውሞ ያላቸው የገበሬዎች አመጽ ይከሰቱ ጀመር። በሸዋ ይፋትና ጥሙጋ አውራጃ የስዲቆ ቀበሌ ገበሬዎች ሚያዚያ 29 ቀን 1950 ዓ.ም ያነሱት አመጽ ለአብነት የሚጠቀስ ነው።[41]

---

[37] ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል "ዝክረ ነገር" 1962 ዓ.ም አዲስ አበባ፤ ገጽ 276–279።

[38] ቃለአብ ታደሠ ሥጋቱ "ሕገ መንግሥት በኢትዮጲያ፡ ከፍትሐ ነገሥት እስከ ኢፌዲሪ" አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር 2011 ዓ.ም። ገጽ 102።

[39] የንጉሠ ነገሥት ብሔራዊ ጦር ማቋቋሚያ ትእዛዝ ቁጥር 21 1951 ዓ.ም፤ ገጽ 7።

[40] ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927 1983" 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት። ገጽ 203።

[41] ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927 1983" 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት። ገጽ 202።

ብሔራዊ ጦር በጠቅላይ ግዛቶችና እንደ አስፈላጊነቱም በሌሎች ቦታዎች የሚቋቋም ሲሆን አባል የሚሆኑት እዲሚያቸው ከ18 ዓመት ያላነሰና ከ25 ዓመት ያልበለጠ ሰዎች ሲሆኑ (ለተጨማሪ አመታት ማገልገል ግን ይቻላል)፤ 1ኛ የማደሪያ መሬት[42] የያዙና ከዚህም ይዞታቸው የተነሳ የወታደራዊ አገልግሎት ተግባር መፈጸም ያለባቸ ሆነው ይህንኑ ተግባር ለመፈጸም በጤናቸው ሁኔታ ምክንያት የማይችሉ ሆነው ያልተገኙ ሰዎች፣ 2ኛ በጤና ማጣት ምክንያት ያለባቸውን የወታደራዊ ተግባር ለመፈጸም ለማይችሉት ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የማደሪያ መሬት ባላቸው ሰዎች ተተክተው ለማገልገል ፈቃደኛ የሆኑትና የክፍለ ግዛቱም ጠቅላይ ገዢ የተቀበላቸው ሰዎች፣ 3ኛ በንጉሠ ነገሥቱ ብሔራዊ ጦር ውስጥ ለማገልገል ፈቃደኛነታቸውን የገለጹና በብሔራዊ ጦር ውስጥ እንዲያገለግሉ የክፍለ ግዛት ጠቅላይ ገዢ ጥያቄያቸውን የተቀበላችው ሰዎች ናችው። የብሔራዊ ጦር ውስጥ የሚያገለግሉ ሰዎች የመጀመሪያውን የውትድርና ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ የተማሩትን ትምህርት ለመከለስና አዲስ ትምህርትም ለመቀበል በየዓመቱ ከሁለት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ልምምድ ያደርጋሉ።

የብሔራዊ ጦር ባገር ግዛት ሚኒስትር የሚመራ ሲሆን፣ በሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ውስጥ በንጉሠ ነገሥቱ የሚሾም የራስ ወይም የደጃዝማችነት ማዕረግ[43] ባለው መኮንን የሚታዘዝ የብሔራዊ ጦር ጠቅላይ መምሪያ ነበር። የንጉሠ ነገሥቱ ብሔራዊ ጦር ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ መኮንንም፤ በብሔራዊ ጦር የሚያገለግሉ በየዓመቱ የሚፈጽሙት የወታደራዊ አገልግሎት ከሁለት ወር የማይበልጥ ሆኖ በየዓመቱ የግብራዊ ተግባር የሚፈጸምበት ጊዜ ልክ፣ ለአገልግሎት የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ ልክ፣ የአገልግሎት ዘመን ልክን በተመለከተ ደንብ እንደሚያወጣ ትእዛዙ ይገልጻል። ያገር ግዛት ሚኒስትሩም ስለብሔራዊ ጦር አቋቋምና አስተዳደር፣ እንደዚሁም ስለተግባሮችና ኃላፊነቶች አፈጻጸም የሚያስፈገውን ደንብ ለማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶታል።

የያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት ብሔራዊ ጦር የሚያዝዘው ግን በጠቅላይ ገዢው ሲሆን ከብሔራዊ ጦር ጠቅላይ መምሪያ መኮንን የሚሰጠውን ትእዛዝ በመከተል ተግባሮችን ያከናውናል። ለእያንዳንዱም ጠቅላይ ግዛት የብሔራዊ ጦር መምሪያ መኮንን ሲኖረው መኮንኑ የደንብ ልብስ ስለመስጠት፣ ስለማሰልጠንና የሠራዊቱን ሥነ ሥርዓት ስለመቆጣጠር ኃላፊ ይሆናል። በተዋረድም የአውራጃ ገዢዎችና በአውራጃው የሚገኙ የብሔራዊ ጦር መምሪያ መኮንኖች ሥራቸውን ያከናውናሉ። የያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት የብሔራዊ ጦርም ተግባሩን የሚያከናውነው በተቋቋመበት ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ብቻ ነው። የብሔራዊ ጦር አባሎችም እንደየደረጃቸው ልዩ ልዩ የማዕረግ ስም[44] የሚሰጣቸው ሲሆን፤ እነሱም ራስ፣ ደጃዝማች፣ ፊታውራሪ፣ ቀኛዝማች፣ ግራዝማች፣ ባላምባራስ፣ መቶ አለቃ፣ ሀምሳ አለቃ፣ እና አሥር አለቃ ነበር።

የብሔራዊ ጦር ተግባሮችም በሰላም ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የፖሊስ ሠራዊት በሚፈጽመው ተግባር ረዳት ይሆናል። ከዚህም በቀር የንጉሠ ነገሥት ብሔራዊ ጦር ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ መኮንን የሚወስነውን ዓይነት ትምህርትና ልምምድ ይከታተላል። በጦርነት ጊዜ ደግሞ የንጉሠ ነገሥት ብሔራዊ ጦር ተግባር የጦር መሣሪያ ቤቶችን፣ ዕቃ ቤቶችን (መጋዘኖችን) ግምጃ ቤቶችን፣ የመገናኛ መስመሮችንና እነዚህን የመሳሰሉ ድርጅቶችን መጠበቅ፣ የጠላት የፓራሹት በራሪዎች በወረዱ ጊዜ ማመልከት፣ የጠላትን የጦር ኃይል መቀነስ፣ ከጠላት የጦር ግንባር በስተኋላ በጠላት ላይ አደጋ መጣልና በጠቅላላውም ስለንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ለመከላከል ከፍ ያለ እርዳታ ማድረግ ነበር።

---

[42] ርስተ ጉልት ወይንም በራስ አገልግሎት የተጐለተ የዘለዐለም ርስት እንዲኾን መንግሥት ፈቅዶለት መሬቱ በርስተ ጉልትነት ተመልምሎ ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ መሬት።

[43] ራስ ቢት ወደድ - ጀነራል፣ ራስ – ሉታኔት ጀነራል፣ ደጃዝማች – ሜጀር ጀነራል፣ ፊታውራሪ፣ ብርጋዴር ጀነራል፣ ቀኛዝማች – ቀኝአዝማች – ኮሎኔል እና ግራዝማች – ሉታኔት ኮሎኖል ማለት ናቸው፡፡
በተጨማሪም ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927 1983" 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት፡፡ ገጽ 17 ላይ ዘርዘር ያሉ የጥንት ማእረጎንች አስቀምጠዋል፡፡

[44] ከአስር አለቃ እስከ ሻምበል ድረስ ያለው የማዕረግ ምልክት በቅርጹ የመደበኛ ጦሩን አይነት ሲሆን በቀለም ግን የመኮንኖች ማዕረግ ምልክት ቀላ ያለ ነሐስ፣ የበታች ሹሞች ደግሞ በአረንጓዴ መደብ ላይ ቀይ ነጠብጣብ ያረፈበት ነው፡፡ የብሔራዊ ጦር አለባበስ ካኪ ኮት፣ ቁምጣና ጥልፍልፍ ሰንደል ቆዳ መጫሚያ፣ እንዲሁም ደማቅ ሰማያዊ መለዮ ሲሆን አርማውም ገበሬ ጠበንጃ አንግቶ ከመኖሪያ ቤቱ አካባቢ በእርሻ ተግባር ላይ እንዳለ በወርቃማ ነሐስ ላይ የተቀረጸና "አገርህን ጠብቅ" የሚል ጽሁፍ ያለበት ነው፡፡ (ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927 1983" 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት፡፡ ገጽ 206፡፡)

የተደራጀው ኃይል ከገበሬው ውስጥ የሚመለመልና የግብርና ሥራውን እያከናወነ ለወታደራዊ ተግባር በሚፈለግበት ወቅት ብቻ በከተት ጥሪ በጦር ሠፈር የሚሰበሰብና የ"ሚሊሻ" ባሕሪ ያለው፣ የመሬት ከበርቴዎች፣ ወይም ልጆቻቸው እሚመሩት ነበር።[45] መቋቋሙ ሲታወጅም በታሕሳስ 15 ቀን 1951 ዓ.ም የተሾሙት ሜጀር ጀነራል ነጋ በደጃዝማች ማእረግ የብሄራዊ ጦር ኤታ ማዦር ሹም፣ ራስ አንዳርጋቸው መሳይ ያገር ግዛት ሚኒስትር ነበሩ። ብርጋዴር ጀነራል ታደሠ ብሩም ከ1956 ዓ.ም ጀምሮ በንጉሠ ነገሥት መንግሥት እስከታሰሩበት እስከ ጥቅምት 1959 ዓ.ም ድረስ የብሔራዊ ጦር ዋና አዛዥ ነበሩ።[46] በ1958 ዓ.ም በሚኒስትር ማእረግ የብሔራዊ ጦር ኤታ ማዦር ሹም የነበሩት ደጃዝማች ከበደ ተሰማ የነበሩ ሲሆን[47] ሌፍተናንት ጀነራል ጃገማ ኬሎም የንጉሠ ነገሥቱ ሥርአት ማብቂያ አካባቢ የብሔራዊ ጦር አዛዥ ነበሩ።[48] ብሔራዊ ጦር ባሉት 14ቱም ጠቅላይ ግዛቶች ያቋቋሚል በአጠቃላይ 14 ብርጌዶች፣ 107 ሻለቆች፣ በ102,601 የሰው ኃይል የተደራጀ ነበር።[49] ገስጥ ተጫኔ እንደሚሉት "የምልመላው ሂደት ከእነዚህ መመዘኛዎች ዝንፍ ብሎ አያውቅም። ምክንያቱም ጭሰኛ ወይም የጭሰኛ ልጆች በውስጡ በዝተው እንዳይገቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ነበረበትና ነው። በዚህ የተነሳ ጭሰኝነት በሚበዛበት የአገሪቱ ግዛት የብሔራዊ ጦር ምልመላና አደረጃጀት ደካማ ነበር።"[50]

## 2.1.2 የንጉሠ ነገሥቱ በሥራ ላይ ያልዋለው "የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት"[51]

የዜግነት ውትድርና እና የዜግነት አገልግሎት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የጦር አገልግሎት፣ ወታደርነት እና የሕዝብ አገልግሎትን የመፈጸም የኢትዮጲያውያን መብትና ግዴታ እንደሆነ በጥቅምት 24 1948 ዓ.ም የተደነገገው ሁለተኛው ተሻሻለው ሕገ መንግሥት አዋጅ አንቀጽ 64 እንዲህ በማለት ያስቀምጣል።

> በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መንግሥት ግዛት የሚኖር ማንኛውም ሰው ሕገ መንግሥቱን፣ ሕጎችን፣ ድንጋጌዎችን፣ ትእዛዞችንና የመንግሥቱን ደንቦች ማክበርና ለእነርሱም መታዘዝ ተግባሩ ነው። ከዚህም በላይ የኢትዮጲያ ዜጎች ለንጉሠ ነገሥቱና ለመንግሥቱ ታማኞች መሆን ግዴታቸው ነው። በንጉሠ ነገሥቱና በመንግሥቱ ላይ ከውጭም ሆነ ከውስጥ የሚነሣውን ጠላት መከላከል፣ የጦር አገልግሎትና በተጠሩም ጊዜ የወታደርነትንና የሕዝብ አገልግሎትን መፈጸም ደግሞም በሕገ መንግሥቱ በተሰጣቸው መብት መሥራት ተግባራቸው ነው።[52]

በዚህም መሰረት ንጉሠ ነገሥቱ "የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት" በሚል በ1965 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 322 አውጀው ነበር።[53] በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስቴርና የጽሕፈት ሚኒስቴር በነበሩት በጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ሥም የወጣው ይህ አዋጅ ያስፈለገበትን ምክንያት ሲጠቅስም "አባቶቻችን በትጋት በብልህነት በአገር አፍቃሪነት በመሥዋዕትነት የአገራችንን አንድነተና ነፃነት ጠብቀው ያቆዩን ስለሆነ፤ ይህን የአባቶቻችንን ትልቅ አደራ ለመጠበቅና ለተከታዩ ትውልድ ለማውረስ እንዲሁም አገራችን የዓለም ሰላም እንዲጠበቅ ለመርዳት ትችል ዘንድ የእያንዳንዱ ዜጋ በውትድርና ዕውቀት በሚገባ መሠልጠን አስፈላጊ ስለሆነ" በማለት ነበር።

---

[45] ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927 -1983" 2006 ዓ.ም፤ አዲስ አበባ፤ ዜድኤ ማተሚያ ቤት፡፡ ገጽ 203፡፡

[46] ኦላና ዞጋ፤ "ግዛትና ግዞት፡ የሜጫ ቱለማ መረዳጃ ማኅበር" አዲስ አበባ፤ 1985 ዓ.ም፤ ገጽ 424፡፡

[47] ደጃዝማች ከበደ ተሰማ "የታሪክ ማስታወሻ" አዲስ አበባ አርክቲክ ማተሚያ 1962 ዓ.ም፡፡ ገጽ 454፡፡

[48] ፍቅረ ማርቆስ ደስታ "ጃገማ ኬሎ፡ የበጋው መብረቅ (የሕይወት ታሪክ)" አዲስ አበባ፤ ሻማ ቢክስ፤ 2001 ዓ.ም፤ ገጽ 214፡፡

[49] ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927 - 1983" 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት፡፡ ገጽ 205፡፡

[50] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 204፡፡

[51] የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት ሰኔ 25 ቀን 1965 ዓ.ም በጠቅላይ ሚኒስትርና የጽሕፈት ሚኒስትር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ስም የታወጀ ሲሆን፤ ከአዋጁ በኋላ የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት በመከላከያ ሚኒስቴር ሥር እንደ አንድ ዘርፍ ተቆጥሮና ተጠሪ መምሪያ ተቋሙሞለት ብ/ጀነራል ታምራት የመምሪያው ኃላፊ ሆነው የተመደቡ ሲሆን ሁሉም ነገር በወረቀት ላይ እንዳለ የየካቲት 1966 ዓ.ም ሕዝባዊ አመጽ ተነሳ፡፡ (ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927–1983" 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት፡፡ ገጽ 524።)

[52] ቃለአብ ታደሠ ሥጋቱ "ሕገ መንግሥት በኢትዮጲያ፡ ከፍትሐ ነገሥት እስከ ኢፌዲሪ" አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር 2011 ዓ.ም፡፡ ገጽ 106፡፡

[53] የብሔራዊ ወታደርነትን አገልግሎት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፤ 1965 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 322፤ ገጽ 150

የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት (Conscription/ National Military Service) እድሚያቸው ከ20 እስከ 21 የሆኑ ወንድ የሆኑ ኢትዮጲያውያን ብቻ የሚመለመሉበት፤ በሶስት አይነት አገልግሎቶች አሉት። አንደኛው ደምበኛ የጦር አገልግሎት (Active Duty) ሲሆን ለወታደራዊ አገልግሎት በመመልመልም ሆነ ወይም በሌላ አኳኋን በጦር ኃይሎች ውስጥ የዝግጁ ተጠባባቂ ጦር ትምህርትን ሳይጨምር አገልግሎት የሚሰጥ ነው። በዚህ አገልግሎት ውስጥ እያንዳንዱ ወጣት ተመልማይ ለሃያ አራት (24) ወራቶች የማገልገል ግዴታ አለበት። ሁለተኛው ዝግጁ ተጠባባቂ ጦር አገልግሎት (Ready Researve Duty) ሲሆን ለደምበኛ የጦር አገልግሎት ወይም በዝግጁ ተጠባባቂነት የጦር ትምህርት ለመፈጸም ዝግጁ የሆነ ነው። ይህ አገልግሎት ለሦስት ተከታታይ አመታት የሚሰጥ ሲሆን በየዓመቱም የአስራ አምስት (15) ቀን ስልጠና ይወስዳሉ። ሦስተኛው የተጠባባቂ ጦር አገልግሎት (Reserve Force Duty) ደግሞ ለደምበኛ የጦር አገልግሎት በሚወሰኑት ሁኔታዎች በተጠራ ጊዜ የሚሰጥ ሲሆን አርባ አምስት አመት (45) አመት እሲከሞላው ድረስ ያገለግላል።

የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት በጦር ኃይሎች ውስጥ ብቻ ሳይሆን *"የመንግሥት መሥሪያ* ቤቶች ሲስማሙ የተመለመሉት ሰዎች በሌሎች ሚኒስቴሮች ወይም የመንግሥት ድርጅት ውስጥ ተመድበው የኢኮኖሚና የማኅበራዊ አገልግሎት ሊፈጽሙ ይችላሉ" በማለት የአዋጁ አንቀጽ 8 ይደነግጋል። በየጊዜው የሚመለመሉትን ወጣቶች ቁጥር የሚወስነውና ድልድልም የሚያካሂደው የአገር መከላከያ ሚኒስትር ሲሆን ሥራቸውን ለቀው የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት የተመለመሉ ወይም የዝግጁ ተጠባባቂነት ጦር ትምህርት እንዲከታተሉ የተመለመሉ ወጣቶች በሥራ ላይ ያሉ ከሆነ ሥራቸውን ለቀው የሚገቡ ሲሆን፤ ሲጨርሱም በተቀጠሩበት ሥፍራ የመመለስ መብት አላቸው። ቀጣሪዎችም የነባርነት መብቱን በተገቢው ሕግና ልማድ መሰረት የማከበር ግዴታ አለባቸው በማለት ደንግጎ ነበር።

### 2.1.2.1 የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ቦርድ [54]

በትእዛዝ ቁጥር 87/1966 ዓ.ም "ሞዓ አንበሳ ዘምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ በአሁኑና በሚመጣው ትውልድ ላይ የተመሠረተውን የሀገራችንን የመከላከያ ኃይል ማጠናከርና እድገቱንም ማፋጠን ምኞታችን ስለሆነ፤ ይህንኑንም ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የሀገራችንን ወጣቶች ለመምራትና ለማስተባበር የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት ቦርዶችን ማቋቋም አስፈላጊ ስለሆነ" በሚል የንጉሠ ነገሥቱ ምክንያት የተቋቋሙት ቦርዶች አንድ "አስተባባሪ ቦርድ" እና በሁሉም ጠቅላይ ግዛቶችና አውራጃዎች ዋና ከተማዎችና በውጭ አገሮች በሚገኙ የኢትዮጲያ ኢምባሲዎች "የምልመላና የምደባ ይግባኝ ቦርድ" ሲሆኑ ቦርዶቹንም እንዲያቋቁም ሥልጣን የተሰጠው የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ነው።

የአስተባባሪ ቦርድ አባላት 1ኛ የአገር መከላከያ ሚኒስትር፣ 2ኛ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር፣ 3ኛ የትምህርትንና የሥነ ጥበብ ሚኒስትር፣ 4ኛ የእርሻ ሚኒስትር፣ 5ኛ የሥራና የውሃ ሀብት ልማት ሚኒስትር፣ 6ኛ የአገር ግዛት ሚኒስትር እና 7ኛ የፕላን ኮሚሽን ጽሕፈት ቤት የበላይ ሹም ናቸው። የቦርዱ ሥልጣንና ተግባርም 1ኛ በኤኮኖሚና በማኅበራዊ ጉዳይ ብቻ የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት ለሚሰጡ ምልምሎች አጠቃላይ ዕቅዶችን ማዘጋጀትና በሥራ ላይ የማዋል እና 2ኛ በልዩ ልዩ የሕዝብ አገልግሎቶችና የልማት ፕሮግራሞች ተመድበው የሚያገለግሉትን ምልምሎች ብዛት መወሰን ናቸው።

በጠቅላይ ግዛቶች የሚገኙ የምልመላና የምደባ ይግባኝ ቦርድ አባሎች 1ኛ የጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴ ወይም ወኪሉ ሊቀ መንበር፣ 2ኛ የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ወኪል፣ 3ኛ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ወኪል፣ 4ኛ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወኪል፣ 5ኛ የእርሻ ሚኒስቴር ወኪል፣ 6ኛ የጠቅላይ ግዛቱ ፖሊስ አዛዥ ወይም ወኪሉ እና 7ኛ የጠቅላይ ግዛቱ የምልመላ መኮንን ናቸው። በየአውራጃው የሚገኙ የምልመላና የምደባ ይግባኝ ቦርድ አባላት 1ኛ የአውራጃው አስተዳዳሪ ወይም ወኪሉ፣ 2ኛ የአውራጃው የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ወኪል፣ 3ኛ የአውራጃው አስተዳዳሪ የሚሰይማቸው የአውራጃው ነዋሪዎች የሆኑ ሁለት ሰዎች ወይም የአውራጃ የውስጥ አስተዳደር በተቋቋመበት አውራጃ ሁለት የአውራጃ አማካሪዎች፣ 4ኛ በአውራጃው የሕዝብ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን የሚወክል አንድ ሐኪም ወይም የሕዝብ የጤና መኮንን እና 5ኛ የአውራጃው የምልመላ መኮንን ናችው።

[54] የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት ቦርዶችን ለማቋቋም የወጣ ትእዛዝ፤ ትእዛዝ ቁጥር 87/1966 ዓ.ም፤ ገጽ 19።

የምልመላና ምደባ ቦርድ ሥልጣንና ተግባር የሚከተሉት ናቸው። 1ኛ ስለ ብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት ሚኒስትሩ የሚሰጠውን መመሪያ ሥራ ላይ የማዋል፣ 2ኛ አዋጁ በሥራ ላይ በዋለበት ቀንና ከዚያም በኋላ 19 ዓመት የሚሞላቸውን ወንዶች ኢትዮጲያውያን ለአገልግሎት የመጥራትና የመመዝገብ፣ 3ኛ የተመዘገቡትን ሰዎች የመመልመልና የመመደብ፣ 4ኛ ሚኒስትሩ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የተመደቡትን ሰዎች የአገልግሎት ጊዜ የማስተላለፍ፣ 5ኛ የተመለመሉትን ሰዎች ወደ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ጣቢያ የመላክ፣ 6ኛ ከሁለት ዓመት ደንበኛ የጦር አገልግሎት ፍጻሜ በኋላ ወደ ተጠባባቂነት የተዛወሩትን የመመዝገብ እና 7ኛ በአዋጁና (አዋጅ ቁጥር 322/1965 ዓ.ም) በዚህ ትእዛዝ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ሥራ ላይ የማዋል ናቸው።

## 2.1.2.2 የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ደንብ[55]

የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት ደንብ፤ በሌ/ጀነራል ከበደ ገብሬ፣ አገር መከላከያ ሚኒስትር ጥቅምት 30 ቀን 1966 ዓ.ም በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 444 በነጋሪት ጋዜጣ የወጣ ሲሆን፤ ምዝገባን በተመለከተ የብሔራዊ ውትድርና አዋጅ ቁጥር 322/1966 ዓ.ም በሥራ ላይ ከዋለበት ቀንና ከዚያም በኋላ 19 ዓመት የሞላው ወንድ ኢትዮጲያዊ የምልመላና የምደባ ቦርድ ጽሕፈት ቤት የምዝገባ ማስታወቂያ ሲወጣ በማስታወቂያው ውስጥ በሚመለከተው ቦታና ጊዜ መመዝገብ ሲኖርበት፣ ደንበኛ የልደት መዝገብ የሌለው ተመዝጋቢም እድሜው በምልመላና ምደባ ቦርድ ተወስኖ ተመዝጋቢው የሚጠየቀውን ቅጽ ይሞላል፣ የምዝገባም ወረቀት ይሰጠዋል። የተመዝጋቢው ማንነት፣ መለያ ቁጥር የተመዘገበበት ጠቅላይ ግዛትና የተወለደበት ዓመተ ምህረት ያለውን የምዝገባ ወረቀት በማናቸውም ጊዜ ይዞ መገኘት አለበት። ተመዝጋቢው የአድራሻ፣ የጋብቻ፣ ወይም የቤተሰብ አቋሙ ሲለወጥ ለምልመላና የምደባ ቦርድ ጽሕፈት ቤት በጽሁፍ የማስታወቅ ግዴታ አለበት።

የብሔራዊ አገልግሎት ጊዜ የሚተላለፍባቸው ምክንያቶችም 1ኛ ከፍተኛ ትምህርት ቤት (ኮሌጅ፣ ዩኒቨርሲቲ፣ ወዘተ) ለመግባት የት/ቤቱን ፈተና አልፎና አስፈላጊውን ሁኔታ አሟልቶ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ እስከ 12 ወር ድረስ፣ 2ኛ በከፍተኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሙሉ ጊዜ ትምህርት የተመዘገበ ትምህርቱን እስካጠናቀቀ ድረስ ወይም 30 ዓመት እስኪሞላው ድረስ ከሁለቱ የሚቀድመውን፤ ሆኖም ከዚያ በፊት ትምህርቱን ያቋረጠ ወይም እንዲያቋርጥ የተደረገ እንደሆነ ለአገልግሎቱ መቅረብ አለበት። 3ኛ ለአገልግሎት እንዲገባ ቢደረግ እናቱ በሞት በተለየችበት ልጁ ወይም ሙሉ ለሙሉ ወይም በይበልጥ በእርሱ በሚተዳደሩ እናቱ ወይም አባቱ ላይ ከባድ ችግር የሚደርስበት ተመዝጋቢ ለሁለት ዓመት፣ ስለሆነም ከሁለት ዓመት በኋላ የተባለው ችግር ያልተቃለለ እንደሆነ የምልመላና የምደባ ቦርድ ሁኔታውን አጥንቶ ለየሁለት ዓመት አገልግሎት የሚሰጥበትን ጊዜ ሊያስተላልፍለት ይችላል፤ 4ኛ ተመዝጋቢው ጊዜያዊ የጤንነት መታወክ የደረሰበት መሆኑ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ባወቀው ሐኪም የተረጋገጠለት እንደሆነ እሲኪድን ድረስ የብሔራዊ አገልግሎት ጊዜው ሊተላለፍለት ይችላል።

ተመዝጋቢዎች የአካል ሙሉነትና የጤና ምርመራ የሚደረግላቸው ሲሆን ለወታደርነት አገልግሎት፣ ለኢኮኖሚ እድገትና ማህበራዊ አገልግሎት ተስማሚ የሆኑ እና ለአግልግሎት ብቁ ያልሆኑትም ይለዩበታል። ማናቸውም ለብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት ከተመለመለ በኋላ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች ውስጥ ተመድቦ የሚሰጠው የኢኮኖሚ ወይም የማኅበራዊ አገልግሎት እንደወታደርነት አገልግሎት የሚቆጥር ሲሆን፣ ሁሉም ተመልማይ አገልግሎት ከመሥጠቱ በፊት የመሰረታዊ የወታደርነት ትምህርት ይወስዳል።

የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ለአገልግሎት በሚገኙበት ጊዜ በየወሩ የኪስ ገንዘብ የሚከፈላቸው ሲሆን፤ የጦር ወይም የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሲታወጅ ለደምበኛ የጦር አገልግሎት የሚጠሩ ዝግጁ ተጠባባቂዎችና ተጠባባቂዎች በዚያኑ ጊዜ ለሌሎች ተመሳሳይ ደረጃ ማዕረግ ላላቸው የጦር ኃይሎች ባልደረቦች የሚከፈለውን ደመወዝና ሌላም ጥቅም ያገኛሉ። የመጓጓዣና ወጪና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችም ይኖሩታል።

## 2.2 በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እና የኢትዮጲያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢሕድሪ) (1966-1983 ዓ.ም) የነበሩ ብሔራዊ አገልግሎት፣ የተጠባባቂ ኃይልና ሚሊሻ ስርዓቶች

[55] የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት ደንብ፤ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 444/1966 ዓ.ም፤ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 2፤ ጥቅምት 30 ቀን 1966 ዓ.ም፤ ገጽ 30።

### 2.2.1 የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ

መስከረም 1 ቀን 1980 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 1/1980 የተደነገገው እና በኢትዮጲያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 26 እንደሚከተለው ነበር። 1ኛ የኢትዮጲያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአገሪቱን የመከላከል ችሎታ ያጠናክራል። 2ኛ የኢትዮጲያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የአርበኝነትና የአብዮታዊ ጀግንነት መንፈስ ዳብራል፤ አገርን ለመከላከል፣ ሕዝብንና አብዮትን ለመጠበቅ፣ እንዳስፈላጊነቱ መላውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ያንቀሳቅሳል። 3ኛ የኢትዮጲያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወጣቱን ሶሻሊስት አርበኝነት ስሜት ያሳድጋል፤ የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎትንም በተግባር ያውላል። 4ኛ የኢትዮጲያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎችን ለመቋቋም ሲቪል መከላከያ ያደራጃል።[56] የሚል ሲሆን በኤርትራ ክፍለ ሀገር በነበረው ግጭትና በሶማሊያ ወረራ ምክንያት የሚሊሻ ምልመላ፣ የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት የተጀመረውና የብሔራዊ አገልግሎትና የሲቪል መከላከል መምሪያ የተቋቋመው ሕገ መንግሥቱ በሥራ ላይ ከመዋሉ ቀደም ብሎ ነበር።

የኢትዮጲያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት (ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ) በ1975 ዓ.ም በኢትዮጲያ ታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ "የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት" ማቋቋሚያ በአዋጅ ቁጥር 238/1975 ዓ.ም ያወጀ ሲሆን፤ የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ማለት የመደበኛ ውትድርና አገልግሎት እና ተጠባባቂ ውትድርና አገልግሎትን በአንድ ላይ ያጣመረ ነበር። አዋጁ ያስፈለገበትም ምክንያት "እያንዳንዱ ኢትዮጲያዊ ሊያገለግል የሚችልበትንና የወረሰውን አንጸባራቂ የአርበኝነት ታሪኩን በሶሻሊስት አርበኝነትና በወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መንፈስ ለማደስ የሚችልበት ብሔራዊ የውትድርና አገልግሎት መመሥረት አብዮታዊ ጦር ኃይሎችን ለማጠናከር፣ አብዮቱን ለመንከባከብና የአብዮታዊት እናት አገርን ነፃነት፣ ሕልውናና የግዛት አንድነት ለመጠበቅ የሚያስችል ጽኑና ቋሚ መሰረት ስለሆነ፤ የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ክንዋኔ የአብዮታዊት ኢትዮጲያ ወጣቶች ለአገሪቱ የኢኮኖሚና የሶሻል እድገት አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚያስችላቸው ስለሆነ" በማለትና ሌሎች ምክንያቶችንም በመጥቀስ አስቀምጦ ነበር።

ብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት የማበርከት ግዴታ ያለበት ማንኛውም እድሜው ከ18 እስከ 50 የሆነ ሲሆን፤ ማንኛውም ዕድሜው ከ18 እስከ 30 ዓመት የሆነ ኢትዮጲያዊ ሁሉ ለመደበኛ ውትድርና አገልግሎት የመመልመል ግዴታ አለበት። የመመልመያ መስፈርቱን የሚያሟላም ከ6 ወር ላላነሰ ጊዜ የውትድርና ትምህርት ተሰጥቶት በመደበኛ የውትድርና አገልግሎት ተመድቦ በአብዮታዊ የጦር ኃይሎች (የምድር ጦር፣ የአየር ኃይል እና የባሕር ኃይል) ወይም በአብዮታዊ ፖሊስ ወይም በአብዮታዊ የጠረፍ ጥበቃ ጦር ለ24 ተከታታይ ወሮች (የሥልጠናው ጊዜ ከ6 ወር የሚበልጥ ከሆነ ያገልግሎት ዘመኑ ይቀነስለታል) ያገለግላል። በሙያ ትምህርት ቤት ወይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጨረሻ ዓመት የተመዘገበ ከሆነ ለአንድ ዓመት፣ ለመመልመል የማያስችል ሕመም ካለበት ህመሙ እሲኪተወው ድረስ የምልመላን ጊዜ ማስተላለፍ ይቻላል።

ሥልጠናውን የፈጸመም ምልምል መመዘኛዎችን የሚያሟላ ከሆነ የተጠባባቂ ጦር መኮንን ሆኖ ለማገልገል የሚያስችለውን ሥልጠና፣ እንዲያገኝ ወደ መኮንኖች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ገብቶ እንዲሰለጥን እድል ሊሰጠው የሚችል ሲሆን፤ ተገቢው ዝንባሌና ችሎታ ያለው ከሆነ የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች፣ የአብዮታዊ ፖሊስ ወይም የአብዮታዊ ጠረፍ ጥበቃ ጦር ቋሚ መኮንን ወይም አባል ሊሆን ይችላል።

ብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት የሰጠ ወጣት አገልግሎቱን ጨርሶ ሲመለስ ቀድሞ ሲሰራበት ወደነበረው የመንግሥት ወይም የሕዝብ ወይም የግል ድርጅት ተመልሶ የመስራት መብት ሲኖረው፤ ለውጭ አገር የትምህርት እድል፣ የሕክምና አገልግሎት፣ የባንክ ብድር የማግኘት ቅድሚያ መብት ይኖረዋል።

የተጠባባቂ ውትድርና አገልግሎት[57] ግዴታ ያለባቸው የመደበኛ ውትድርና አገልግሎት የሰጠ ማንኛውም ግለሰብ እድሜው 50 ዓመት እስኪሞላው ድረስ እና ማናቸውም ጡረታ የወጣ የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች፣ የአብዮታዊ ፖሊስ ወይም የአብዮታዊ ጠረፍ ጥበቃ ጦር አባል ጡረታ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ተከታታይ ዓመታት

---

[56] ቃለአብ ታደሠ ሥጋቱ "ሕገ መንግሥት በኢትዮጲያ፡ ከፍትሐ ነገሥት እስከ ኢፌዲሪ" አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር 2011 ዓ.ም። ገጽ 233።

[57] የብሐራዊ ውትድርና አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 238፤ 1975 ዓ.ም፤ ገጽ 37።

ሆኖም እድሜው 50 ዓመት እስኪሞላው ድረስ ሲሆን፤ ዋና ተግባሩም መንግሥት ጥሪ በሚያደርግበት ቦታና ጊዜ ተገኝቶ የውትድርና አገልግሎት ማበርከት ነው።

የተጠባባቂ ውትድርና አገልግሎትን እያከናወነ ያለ ግለሰብ በሥራ ላይ ከሆነ አሠሪው አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ደመወዙን የመክፈል፣ የጡረታና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችንና መብቶቹን የመጠበቅ ግዴታ እንዳለበትም አዋጁ ያስቀምጣል። አዋጁ ከ"ብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት" እና ከ"ተጠባባቂ ውትድርና አገልግሎት" በተጨማሪ "የቅድመ-ምልመላ ወታደራዊ ትምህርት" እድሚያቸው 16-30 ዓመት የሆኑ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር በሚወስነው መሰረት ለቅድመ ምልመላ ሥልጠና መመዝገብ እንዳለባቸው፤ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በየጊዜው አጠቃላይ ወታደራዊ ትምህርት እንደሚሰጣቸውም ይደነግጋል።

## 2.2.2 ሚሊሻ

የደርግ ወታደራዊ መንግሥት ሥልጣን በያዘ ማግሥት በ1960ዎቹ አጋማሽ ላይ እና "የገበሬዎች ሚሊሻ" እና "የሰራተኞች ሚሊሻ" በማቋቋም የሶማሊያ ወረራ እንደመከቱ አድርጎ የነበር ሲሆን፤[58] የ"እናት አገር ጥሪ" በሚል እነዚህ በየክፍል ሀገሩ ይሰለጥኑ የነበሩ ሚሊሺያዎች እንደተጠባባቂ ኃይል ተደርገው ይታዩ እንደነበርና የአካባቢያቸውን ሰላም ከማስጠበቅ ያለፈ በኢትዮ-ሶማሊያ ጦርነት እንዲዘምቱ ተደርገው ክፍተኛ መስዋትነት የከፈሉን በጀግንነት የአገራቸውን ዳር ድንበር አስከብረው ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱ ተደርገዋል።[59] በወቅቱ የደርግ ሊቀመንበር የነበሩት ሌ/ኮሎኔል መንስቱ በጦርነቱ ዘማች የነበሩ ሚሊሻዎች 300,000 የሚሆኑ እድሚያቸው ከ18 እስከ 40 የሆኑ ወንዶች እንደነበሩ ይገልጻሉ።[60]

በደርግ ሥርዓት ግን በጣም ታዋቂ የነበረው የሚሊሻ ስርዓት በ1970ዎቹ አጋማሽ የተጀመረው የክፍለ ሀገር፣ የአውራጃ እና የወረዳ "የአብዮት ጥበቃ" ኮሚቴ ነበር።[61] "ሚሊሻ" የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ግዜ በመንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ውስጥ በይፋ ጥቅም ላይ የዋለው ደገሞ በ1965 ዓ.ም በወታደራዊ ኮሚሳሪያትና የአካባቢ ሕዝባዊ ሠራዊት ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ በአማርኛ "አካባቢያዊ ሕዝባዊ ሠራዊት" የሚለውን ቃል ለመተካት "Territorial People's Militia" በሚል በእንግሊዜኛ የተጻፈው የአዋጁ ክፍል ውስጥ ነበር።[62]

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ወደ ሥልጣን እንደመጣ ያደራጀው የመጀመሪያው 'የሚሊሻ ሥርዓት' "የገበሬዎች የጥበቃ ጓድ" የሚባል ነበር።[63] በወቅቱ በየአካባቢያቸው የገበሬዎች ማኅበራት ራሳቸውን የማስተዳደርና የተወሰኑ የወንጀል እና የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን ለመፍታት የሚያስችል ተቋማትን ያቋቋሙ ሲሆን የጥበቃ ጓድ የገባሬ የአካባቢ ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎችን በማስፈጸም፣ በተጨማሪም ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን ደኖችን፣ ማእድን ማውጫዎችን፣ ድልድዮችን፣ ሰብሎች እና ሌሎች ንብረቶችን ይጠብቃል። የጥበቃ ጓዶች ገበሬው ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆነ መሪ ሲኖራቸው የአገልግሎት ዘመናቸውም ለሁለት ዓመታት ነበር። የጥበቃ ጓድ አባል ለመሆን የተሚላ ጤንነት ያለው፣ የአልኮል ወይም የሌሎች

---

[58] Adane K Bezabih: The Role of Workers Militia in the Ethio-Somalia War, 1977-78. Munich Personal RePEc Archive, 2022. Online: https://mpra.ub.uni-muenchen.de/115272/

[59] ከሌ/ኮሎኔል ፍስሃ ደስታ፣ የኢህዴሪ ም/ፕሬዚዳንት ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፤ አዲስ አበባ፤ ሚያዚያ 21 ቀን 2014 ዓ.ም።

[60] መንግሥቱ ኃይለማርያም፤ ትግላችን የኢትዮጲያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ፤ አዲስ አበባ፤ ፀሐይ አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅት፤ 2004 ዓ.ም:: ገጽ 389::

[61] የገበሬ ማኅበራትን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 223/1974 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ::

[62] ወታደራዊ ኮሚሳሪያትና የአካባቢ ሕዝባዊ ሠራዊት ማቋቋሚያ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 239/1975 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ::

[63] የገበሬዎች ማኅበር ማደራጃና ማጠናከሪያ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 71/1968 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ::

አደገኛ ነገሮች ሱሰኛ ያልሆነ፣ በአካባቢው የተመሰገነ፣ በስርቆት ወንጀል ተከሶ ያልተፈረደበት እና እድሜው ከ21 ዓመት በላይ የሆነ ነበር።[64]

በ1974 ዓ.ም መንግሥት የገበሬ ማኅበራትን ሥልጣን በማጠናከር የቀበሌ ገበሬ ማኅበር፣ የክፍለ ሀገር፣ አውራጃና ወረዳ የገበሬ ማኅበራትን አቋቋመ።[65] ይህም ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ "የገበሬዎች የጥበቃ ጓድ" የሚለውን በመቀየር "የአቢዮት ጥበቃ ኮሚቴን" የሚባለውን ሁለተኛውን 'የሚሊሻ ሥርዓት' አቋቋመ። ዋናውን የማህበረሰቡ 'ጥበቃ'[66] የሚያከናውኑት የቀበሌ አብዮት ጥበቃዎች ሲሆኑ የአብዮት ጥበቃ ዋና ዋና ሥልጣን እና ተግባራት "በኢትዮጲያ አብዮት፣ አንድነትና ነፃነት ላይ የሚጠነሰሰውን የፖለቲካ ወንጀል የመከታተልና ለማኅበሩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የማሳወቅ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካገኘው ወይም ወንጀል ፈጻሚው ይሰወራል፣ ማስረጃ ያጠፋል፣ አደጋ ያደርሳል ለማለት አጥጋቢ ምክንያት ሲኖር ይዞ ለአቅራቢያው ፖሊስ ጣቢያ የማስረከብ፤ በሕግ መሰረት ከገበሬ ማሕበር ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም ከፍርድ ሸንጎ በሚሰጠው ትእዛዝ መሰረት ተፈላጊ ሰዎችን የማቅረብ፣ የፍርድ ሸንጎን ውሳኔና ትእዛዝ የማስፈጸም በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የደንን ማዕድንን ድልድዩን ሰብልን ወይም በየጊዜው እንዲጠበቁ የሚወሰኑትን የሕዝብና የመንግሥት ንብረቶችን የመጠበቅ እና ሌሎች የጥበቃና የጸጥታ ተግባር የማከናወን ነበር።

በሦስተኛ ደረጃ የተቋቋመው "ሕዝባዊ ሠራዊት" ወይም ሚሊሻ ሲሆን[67] በወረዳ፣ በአውራጃና በክፍለ ሀገር እንዲሁም በከተሞች የተቋቋመ ነበር። የአካባቢ ሕዝባዊ ሠራዊት አላማ "የሰፊው ሕዝብ ሰላምና ደህንነት አስተማማኝ መሆኑን ለማረጋገጥና የሶሺዮ-ኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን ያለስጋት ለማከናወን ይችል ዘንድ ለአብዮቱና ለአገሪቱ አንድነትና ነጻነት ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ የውስጥና የውጭ ጠላቶችን መዋጋት፣ ሰፊውን ሕዝብና የመንግሥትንና የሕዝብን ንብረቶች ከተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ መከላከል ይሆናል።"[68] ተግባርና ኃላፊነታቸውም ከውጭ የሚዘነዝርን ጥቃትና ወረራ መከላከል፣ ከውስጥ ጸረ አብዮትና ጸረ አንድነት የሚደርሱ ጥቃቶችን መካለካለና የመንግሥትን የሕዝብ ንብረትን ከተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች መከላከልና የመሳሰሉት ናቸው። ከቀድሞው የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ብሔራዊ ጦር በተለየ ይህ ሚሊሻ ከአካባቢው ክፍለ ሀገር ውጪ ሊሰማራ የሚችልና ከመደበኛው ሰራዊት ጋር አብሮ ለግዳጅ የሚሰለፍ ነበር

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግሥት ወቅት ከብሔራዊ ወታደራዊ አገልግሎት እና ሚሊሻ ጋር በተያያዘ በጣም አስፈላጊው ተቋም ወታደራዊ ኮሚሳርያት ነበር።[69] የወታደራዊ ኮሚሳርያት ዋና ተግባርና ኃላፊነትም ለአካባቢ ሕዝባዊ ሠራዊት (ሚሊሻ) አባልነት፣ ስልጠና፣ ሥምሪት፣ የደንብ ልብስ፣ ትጥቅና የሚሳሰሉትን መመሪያዎች ማዘጋጀት እና የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት አዋጅ በሥራ ላይ መዋሉን መከታተል፣ እንዲሁም ለክተት የሚያስፈልገውን ንብረትና የሰው ኃይል መመዝገቡን ይከታተላልና መቆጣጠር ነበር። ወታደራዊ ኮሚሣሪያት በከተማ፣ በወረዳ፣ በአውራጃና በክፍለ ሀገር ደረጃ ጽ/ቤቶች ሲኖሩት ዋናው የወታደራዊ ኮሚሳሪያት ጽ/ቤት በአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ውስጥ ተቋቁሞ፤ ዋናው ወታደራዊ ኮሚሣርም የምክትል ሚኒስትር ደረጃ ነበረው።[70]

---

[64] ዝኒ ከማሁ፡፡

[65] የገበሬ ማኅበራትን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 223/1974 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፡፡

[66] የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት እንዲያስጠብቁ እንዲያስጠብቁ ቢመረጡ የቀበሌ አብዮት ጥበቃዎች በዚህ ወቅት የሚታወቁበት ዋናው መለያቸው ግን የደርግ ሥርዓትን የሚቃወሙት ላይ ከፍተኛ የሆነ ግፍ መፈጸም ነበር፡፡ ስለ አብዮት ጠባቂዎች የሚከተሉትን መጽሐፍት መመልከት ይቻላል፡፡ ገነነ መሙሪያ፤ ኢህአፓ እና ስፓርት ክፍል 1፤ አዲስ አበባ፤ 2006 ዓ.ም፡፡ ገጽ 14-17፡፡ ክፍሉ ታደሰ፤ ያ ትውልድ የለውጥ ማዕበል በኢትዮጲያ፤ ቅጽ ሁለት፤ አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች፤ 1991 ዓ.ም፤ ገጽ 72-73፡፡

[67] ወታደራዊ ኮሚሳሪያትና የአካባቢ ሕዝባዊ ሠራዊት ማቋቋሚያ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 239/1975 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፡፡

[68] ዝኒ ከማሁ፡፡

[69] ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927 1983" 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት፡፡

[70] ወታደራዊ ኮሚሳሪያትና የአካባቢ ሕዝባዊ ሠራዊት ማቋቋሚያ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 239/1975 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፡፡

### 2.2.3 የእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ

ወታደራዊም ባይሆን በኢትዮጲያ ታሪክ ትልቅ የሆነ የሕብረተሰብ ተሳትፎ የታየበትና ውጤታማ የሆነ "የብሔራዊ አገልግሎት" የ1967 ዓ.ም የታወጀው "የእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ" ነበር።[71] ዘመቻው በአዋጁ መግቢያ እንደተገለጸው አዋጁ ለመታወጅ ያስፈለገበት መክንያት እነደሚከተለው ነበር።

> "የኢትዮጲያ ሕዝብ በጨቋኝ መኳንንት፣ መሳፍንት ከበርቴ፣ በተጨቋኝ ላብ አደር ሠራተኛ ገበሬ ስርዓቶችና መደቦች እንዲሁም የአገሪቱ አስተዳደር በቆሮቋዥ ገጠርና በታዳጊ ከተማ ተክፍለው በነዚህ መካከል የኑሮ ደረጃ መራራቅ እየሰፋ በመሄዱ፤ የኢትዮጲያ ሕዝብም እርስ በርስ እንዳይገናኝ፣ እንዳይፈ.ቃቀርና እንዳይተባበር ብዙ የሚለያዩ ገደቦች በመደረጋቸው፤ ሕዝቡም ተባብሮ ችግሩን እንዳያስወግድ ግለሰቡ ራሱን ወዳድና ከራስ በላይ ንፋስ በሚል ፍልስፍና እንዲያምን በመደረጉ፤ ኢትዮጲያ ትቅደም[72] በሚለው ፍልስፍና መሠረት ይህ ሁኔታ መቀጠል የሌለበት በመሆኑ፤ ትምህርትም አስተማሪ በክፍል በሚያስተምረውና ተማሪው በቃሉ በሚያጠናው ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ከሥራ ጋር ሲዋሐድ እውነተኛ ትምህርት እንደሚሆን በማመን፤ በመተማና በገጠር ነዋሪዎች መካከል ያለውን የንሮ ደረጃ ልዩነት ለማጥበብ በአካባቢው የሚገኙትን ሰዎች በማስተባበር በተጨማሪም በወጣቱ እውቀት በመጠቀም የገጠሩን ንሮ ማሻሻል የኢትዮጲያ ትቅደም ፍልስፍና ዓይነተኛ ዓላማ በመሆኑ፤ ይህንንም ከግቡ ለማደረስ የአስተሳሰብ ለውጥ ማስገኘት አስፈላጊ ስለሆነና ለዚሁም ተግባር ተማሪና አስተማሪ ሌሎቹም ጭምር መሰለፍ ያለባቸው መሆኑን በማመን . . ."[73]

ከዘመቻው አላማዎችም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤ የኢትዮጲያ ትቅደም ዓላማን ሕዝቡ በሚገባ እንዲያውቀው በማድረግ፤ የማንበብና የመጻፍ እንዲሁም መሰረታዊ የሆኑ የርሻ የጤና የቴክኒክና ሌሎችንም የማኅበራዊ ኑሮ ነክ ትምህርቶችንለሰፊው ሕዝብ ማዳረስ፤ ስካርን፣ ዝሙትን፣ አድልዎን፣ ሐቀቢስነትንና እነዚህንም የመሳሰሉት የሞራል ውድቀትና ጠንቆች መሆናቸውን ማስረዳትና የክብረ ኅሊና ተሐድሶ እንዲገነባ መጣር፤ እያንዳንዱ ዜጋ ለአገሩ አንድነተና እድገት እኩል አላፊነት እንዳለበት ማስተማር፤ አንዱ ሌላውን በትውልዱ፣ በሀብቱ፣ በሥልጣኑና በዕውቀቱ የበላይነት ተፅዕኖ ሊያደርግበት የማይችል መሆኑን ማሳመን፤ በድርቅ ምክንያት የደረሰውን የረኃብ ችግር ለመቋቋምና ወደፊትም እንዳይደርስ በሚያደርገው ትግል ተካፋይ መሆን እና የሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብትና የሰው ኃይል በበለጠ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ ለማስገኘት መሪ ጥናትና መረጃዎች መሰብሰብ ነበር።

ዘመቻው በዋናነት ስምንት ፕሮግራሞች ነበሩት። 1ኛ የኢትዮጲያ ትቅደምን ዓላማ በዝርዝር ማስረዳት፣ 2ኛ የመሰረተ ትምህርት ማለትም ፊደል አስቆጥሮ ንባብና ጽሕፈት እንዲሁም በአኃዝ አማካኝነት ሂሳብ ማስላትን ማስተማር፣ 3ኛ የልማት መሰረቶችና የኑሮ ማሻሻያ ዘዴዎችን ማስተማር፣ 4ኛ የገጠሩ ገበሬ በተሻሻለ የእርሻ ዘዴና ቴክኒክ በመጠቀም የኑሮ ደረጃውን ከፍ እንዲያደርግ በሥራ ጭምር ማስተማር፣ 5ኛ ስለ መሬት ይዞታ ስሪት ያለውን ችግርና ስለዚሁ ጉዳይ የሚወጣውን አዋጅ ማስረዳት፣[74] 6ኛ መሠረታዊ የሆኑ የጤና ጥበቃ አገልግሎቶችና ትምህርት መስጠት፣ 7ኛ የባህል ቅርሶችን መሰብሰብና ማሳወቅ እና 8ኛ ለእድገት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ ናቸው።

---

[71] የዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ለማድረግ የወጣ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 11/1967 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፡፡

[72] ኢትዮጲያ ትቅደም የሚለው ፍልስፍና ህብረተሰባዊነት ወይም የኢትዮጲያ ሶሻሊዝም ማለት ሲሆን (Provisional Military Administrative Council (PMAC): Declaration of the Provisional Military Government of Ethiopia. Addis Ababa, Berhanena Selam Printing Press, 1974.) ደረግ በወቅቱ እራሱን በአፍሪካ የምክሲዝም ሌኒንዝም አራማጅ አድርጎ ይቆጥር እንደነበረ አንዱ ማሳያ ነው። የኢትዮጲያ ሶሻሊዝም የመጣው የታንዛኒያውን 'አፍሪካዊ ሶሻሊዝም' እንደ ሞዴል በመውሰድ ነበር፡፡ (ፍቅረሥላሴ ወግደረስ፤ አብዮቱና ትዝታዬ፤ አዲስ አበባ፤ ፀሐይ አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅት፤ 2008 ዓ.ም፡፡

[73] ዝኒ ከማሁ፡፡

[74] የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 31/1967 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፡፡

የዘመቻው ተካፋይ የነበሩትም በ1966 ዓ.ም የትምህርት ዘመን መጨረሻ ወደ 11ኛና 12ኛ ክፍል የተዛወሩ ወይም መዛወር ይገባቸው የነበሩት የቀለምና የአጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የንግድ ሥራና የተግባረ እድ የምህርት ቤት፣ የነርሶች፣ የኪነ ጥበብና የእርሻ ትምህርት ቤት እንዲሁም የፖሊቴክኒክና የመምህራን ማሰልጠኛ ኢኒስቲትዩት ተማሪዎችና የነዚሁ ክፍሎች መምህራን፤ በ1966 ዓ.ም መጨረሻ የ12ኛን ክፍል ብሔራዊ ፈተና የወሰዱ ወይም መውሰድ ወይም መውሰድ ይገባቸው የነበሩት ተማሪዎች እና በዩኒቨርስቲ፣ በኮሌጅና በመለስተኛ ኮሌጅ ደረጃ ያሉ ተማሪዎችና መምህራን ነበሩ። ዘመቻው በነሐሴ 1967 ዓ.ም የዘመቻው "ተካፋዮች ከገናቸው እንዳይለዩና ርዳታቸውም እንዳይቋረጥባቸው የዘመቻው ተጠቃሚ የሆኑት በየጊዜው አጥብቀው የሚጠይቁ ስለሆነ" በሚል ምክንያት እና የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ንብረት ለማድረግ የወጣውን አዲስ አዋጅ[75] ትግበራ ለማገዝ እስከ ሰኔ 1968 ዓ.ም ድረስ እንዲራዘም ሆኖ ነበር።[76] በዘመቻው 60,000 የሚሆኑ ተማሪዎች የተሳተፉ ሲሆን፤[77] የዘመቻው ቁልፍ ውጤት የነበረው የመሰረተ ትምህርት በማስተማር ከ350,000 በላይ የሆኑ አርሶ አደሮችን ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ ማድረግ ነበር።[78]

## 2.3 በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክሲያዊ ሪፐብሊክ በሥራ ላይ ያለውን የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል እና የክልል የሚሊሻ ሥርዓት

### 2.3.1 በ1995 ዓ.ም የተቋቋመው የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል

በ1995 ዓ.ም የተቋቋመው "የተጠባባቂ ኃይል" ሦስት አላማዎች ኖረውት የተቋቋመ ሲሆን፤ እነሱም "የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከማንኛውም አደጋ በአስተማማኝ ለመጠበቅ፣ በጦረነት ወይም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመከላከያ ሠራዊቱን ተቀላቅሎ ለመሠማራት፣ እና ሰው ሠራሽም ሆነ ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ሲከሰቱ ፈጥኖ በቦታው ላይ በመገኘት ዕገዛ ወይም እርዳታ ለመስጠት ነው።[79] ተጠሪነቱ ለአገር መከላከያ ሚኒስትር ሥር የሆነው ይህ ኃይል አደረጃጀቱም፤ በአዋጁ መሰረት፣ ተጠባባቂ ኃይሉን የሚያደራጀና የሚያስተባብር ቢሮ በሚኒስቴር መሥሪያቤቱ ሥር በአዲስ አበባ የሚኖረው ሲሆን፣ በሁሉም የኢትዮጲያ ክልሎች ከክልል መስተዳደሮች ጋረ ተቀናጅተው የሚሰሩ የላይዘን ጽሕፈት ቤቶች እንዲኖሩት ደንግጓል። በተጨማሪም የተጠባባቂ ኃይሉ በወረዳ ደረጃ በአሃድ ተዋቅሮ እንደሚደራጅና በመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ በግል ተቋማት፣ እና በሕዝባዊ ማህበራት ውስጥ የላይዘን ጽሕፈት ቤቶች ሊኖሩት እንደሚችሉ አዋጁ ቢደነግግም፤ በተግባር ደረጃ ግን የላይዘን ጽሕፈት ቤቶች ያሉት በዞን ደረጃ ብቻ ነው።

የምልመላ መስፈርት በተጠባባቂ ኃይሉ የሚያደራጀና የሚያስተባብር ቢሮ በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን መሆኑን የአዋጁ ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 የሚደነግግ ሲሆን፤ እስካሁን አዋጁ ከወጣበት ጀምሮ የተጠባባቂ ኃይል ምልመላ የሚደረገው ከአዲስ አበባ ከተማ በስተቀር በሁሉም ክልሎችና ድሬዳዋ ሲሆን ሁሉም ተጠባባቂ የምድር ኃይል ወይም 'እግረኛ' እና በአብዛኛው ካርሶ አደሩ መህበረሰብ ነው። የምልመላ መስፈርቱም ለመደበኛ ሠራዊት በተዘጋጀው መስፈርትና የሚሊሻ አባላት የአገልግሎት ዘመንም ለ7 ዓመት ነው። ወታደራዊ ስልጠናን አስመልክቶ አዋጁ ተጠባባቂ ኃይሉ ወደ ማሰልጠኛ ማዕከላት በመግባት መሰረታዊ ወታደራዊ ስልጠና እንደሚሰጠው፣ የምግብ የአልባሳት፣ የኪስ ገንዘብ፣ የህክምናም የትምህርት መርጃ እቃዎችን በነጻ እንደሚያገኝና ሲያጠናቅቅም የምስክር ወረቀት ተሰጥቶት ወደ አካባቢው እንደሚመለስ፣ በየዓመቱም ከመከላከያ ሠራዊቱ ጋር የማጠናከሪያ ሥልጠናና ልምምድ እንደሚሰጠው ይደነግጋል። አዋጁ ከወጣ በኋላ ለነበሩት 10 አመታት አካባቢም በመቶ ሺዎች

---

[75] የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ንብረት ለማድረግ በወጣ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር47/167፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፡፡

[76] የእድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ጊዜን ለማራዘም የወጣ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 48/1967 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፡፡

[77] Dawit WoldeGiorgis: Red Tears: War, Famine and Revolution in Ethiopia. New Jersey, The Red Sea Press, Inc., 1989.

[78] Paulos Milkias: Zemecha: Assessment of the Political and Social Foundations of Mass Education in Ethiopia. Northeast African Studies, Spring 1980, Vol. 2, No. 1 (Spring 1980). 19-30.

[79] የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ማቋቋሚያ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 327/1995 ዓ.ም፤ በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክሲያዊ ሪፐብሊክ፡፡

የሚቆጠሩ የተጠባባቂ ኃይል አባላት በመሰልጠን አገልግሎት የሰጡ ሲሆን በቀጣይ አመታት ግን ሥልጠናም ሆነ ምልመላ እጅጉን ተቀዛቅዞ ቆይቷል።

ማዕረግን በተመለከተ አዋጁ የተጠባባቂ ኃይል አባል ከሰራዊቱ ጋረ ተቀላቅሎ አገልግሎት በሚሰጥበተ ጊዜ በመከላከያ ሠራዊት መመሪያ መሰረት የማዕረግ እድገት እንደሚያገኝ የሚደነግግ ሲሆን፣ "በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ለዕዝና ቁጥጥር የሚያስፈልጉ የኃላፊነት ደረጃዎች እየተጠኑ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ማዕረጎች ሊሰጡ ይችላሉ"[80] ይላል። ነገር ግን እስካሁን ድረስ የተጠባባቂ ኃይል አባላት የራሳቸው የሆነ ወታደራዊ ልብስ ቢኖራቸውም ማእረግ ግን የላቸውም።

ከመንግሥት ሪፎርም በኋላ በ2012 ዓ.ም የወጣውና በኢህአዴግ በሥልጣን በቆየባቸው አመታት የመከላከያ ሠራዊት የፖለቲካ መመሪያ እየነበረው "የሰራዊት ግምባታ በአቢዮታዊ ዴሞክራሲ" ወይም በተለምዶ "ቀዩ መጽሐፍ" የሚባለውን የተካው "የኢፌዴሪ የመከላከያ ሠራዊት ግንባታ ስትራቴጂ" ሰነድ ለተጠባባቂ ኃይል ግምባታ እንደሚከተለው ትኩረት የሰጠ ነው።

> ተጠባባቂ ጦር በመደበኛ የጦርነት ግዳጅ ውስጥ ያልተሰማራ ነገር ግን መደበኛ ሥልጠና ተሰጥቶት ለግዳጅ በሚፈለግበት ጊዜ ጥሪ ለግዳጅ ዝግጁ መሆን የሚችል ኃይል ነው። ተጠባባቂ ጦር ሀገራዊ የኢኮኖሚ አቅምን ሳይጎዳ ብቁ የውጊያ ክህሎት ያለው የሰው ኃይል ለማደራጀት የሚቻልበት አደረጃጀት ነው። ተጠባባቂ ጦር በሰላም ወቅት በቀላል ወጭ ሀገራዊ ጦርነትን የማስቀረት አቅማችንን በማጎልበት ጦርነትን የማስቀረት አቅም የሚያሳድግ ነው። ተጠባባቂ ጦር በጦርነት ወቅት መደበኛውን የመከላከያ ሠራዊት የሰው ኃይል ዐቅም በማጠናከር ከፍ ያለ ሚና ይጫወታል።በአደጋ ወቅት የአደጋ መከላከልና የጸጥታ ግዳጆችን መደበኛውን ሠራዊት ተክቶ ይፈጽማል። በዚህም መደበኛው ጦር በሌሎች ወሳኝ ግዳጆች ላይ እንዲያተኩር ዕድል ይፈጥራል። በመሆኑም ወቅታዊና የቅርብ ጊዜ የሥጋት ምንጮችን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ተጠባባቂ ጦርን የማሠልጠንና የማደራጀት ሥራዎች ተጠናክረው ይሠራሉ።[81]

## 2.3.2 ሚሊሻ

በኢትዮጲያ የሚሊሻ አገልግሎት በክልል ስር የሚገኝ የጸጥታ አደረጃጀት ሲሆን፤ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ ጽ/ቤቶች ያሉት ነው። ለምሳሌ በ1997 ዓ.ም የወጣው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የሚሊሺያ አስተዳደርና አደረጃጀት ሥርዓት ደንብ "ሚሊሺያ" ማለት ከምርት ተግባሩ ሳይነጠል በህዝብ የተመረጠና ምንም አይነት የደመወዝ ክፍያ የማያገኝ ታጣቂ ነው በማለት ይገልጸዋል።[82]

የአካባቢ ሚሊሻ ኃይል የአካባቢ ሚሊሻ የአካባቢን ደህንነትና ጸጥታ ለማስፈን የራሳቸውን ድርሻ በመውሰድ የሀገር ውስጥ ሰላምን ለማስፈን ከሀገር መከላከያ ሠራዊትና ከሌሎች የደህንነትና የጸጥታ ኃይሎች ጎን በመሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ኃይሎች ናቸው።[83] እነዚህ ኃይሎች በይበልጥ በአካባቢያቸው ከሚገኝ የፖሊስ ኃይል ጋር በመሆንና ተቀናጅቶ በመስራት ወንጀልና የሕዝቡን ሰላም የሚነሱ እንቅስቃሴዎችን ይከላከላሉ። የአካባቢ ሚሊሻ ኃይል በአካባቢው በሚገኝ የመከላከያ ሠራዊት ማሰልጠኛ ተቋም በመግባት አስፈላጊና ለተልዕኳቸው ተገቢ የሆነ ስልጠና በመውሰድ ጸጥታን ለማስከበር በህብረተሰቡ ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ፤ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ተቋምም እንደ አስፈላጊነቱ ተገቢውን ቁሳዊና ቴክኒካዊ እገዛዎች ያደርግላቸዋል።[84] የአካባቢ ሚሊሻ ኃይሎች በማህበረሰቡ ውስጥ በመሆን በአካባቢያቸው በሚደረጉ ማንኛውም የልማት እንቅስቃሴዎች ከህብረተሰቡ ጎን በመሰለፍ

---

[80] አንቀጽ 17/2።

[81] "የኢፌዴሪ የመከላከያ ሠራዊት ግንባታ ስትራቴጂ" የካቲት 2012 ዓ.ም፤ ገጽ 74 – 75፡፡

[82] የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የሚሊሺያ አስተዳደርና አደረጃጀት ሥርዓት ደንብ፤ ቁጥር 28/1997 ዓ.ም፡፡

[83] የጦር ኃይሎች ጠቅላይ መምሪያ "የኢፌድሪ መከላከያ ሚኒስቴር የሠራዊት ተልዕኮ" መስከረም 2002 ዓ.ም፤ ገጽ 60፡፡

[84] ዝኒ ከማሁ፡፡

አጠቃላይ ማህበራዊ ኑሯቸውን ይመራሉ። አስፈላጊ በሆኑ የአካባቢ ሰላምና ጸጥታ የማስከበር ስራዎች ላይ ግዳጃቸውን ይፈጽማሉ።

በኢትዮጲያ የሚሊሺያ አባል የሚሆን ሰው በአካባቢው በሕዝብ የሚመረጥ ሲሆን ከዚህ በታች የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ሰው የሚሊሺያ አባል መሆን ይችላል። ሀ. ዜግነት ኢትዮጲያዊ የሆነ፣ ለ. ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ ከ50 ዓመት ያልበለጠ፣ ሐ. ለኢ.ፌዴ.ሪና ለክልል ህገ-መንግስት መሰረታዊ መርሆዎች ተገዥ የሆነ፣ መ. በሚኖርበት አካባቢ ሕዝብ መሀል በመልካም ሥነ-ምግባሩ የሚታወቅ፣ ሠ. ቋሚ የመተዳደሪያ ገቢ ያለው፣ ረ. በማናቸውም ፀረ- ሕዝብ ተግባራት ያልተሰማራና በወንጀል የጥፋተኛነት ሪኮርድ የሌለበት፣ ሰ. ለሚሊሻ አባላት የሚሰጠውን ሥልጠና ለመከታተል ፈቃደኛ የሆነና ስልጠናውን በአግባቡ ተከታትሎ የወሰደ፣እና ሸ. ለወታደራዊ እንቅስቃሴ ብቃት ያለው።[85]

የሚሊሻ አባል ግዴታና ኃላፊነቶችም 1. የአገርን ሉአላዊነትና ህገ- መንግስታዊ ሥርዓቱን ከማንኛውም የውስጥና የውጭ ጣላቶች የመጠበቅ፣ 2. በህገ-መንግስቱ የተረጋገጠ የዜጎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ማክበርና የማስከበር፣ 3. የሚሰጠውን ተገቢ የሥራ ተልዕኮ በተወሰነው ጊዜ አጠናቅቆ ለበላይ ኃላፊ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ሪፖርት የማድረግ፣ 4. አስፈላጊውን መረጃ የመጠየቅ የመቀበል፣ 5. የአካባቢውን ሕዝብ ፀጥታ አደጋ ላይ የሚጥሉ መረጃዎች ሲደርሱት ወዲያውኑ ባገኘው ፈጣን የመገናኛ ዘዴ ለበላይ አካል የማስተላለፍ፣ 6. ሕዝብ በሚያካሂዳቸው የልማት ስራዎች ግንባር ቀደም በመሆን አካባቢውን የማልማት፣ 7. ከፖሊስና ከመከላከያ ሰራዊት ጋር ተቀናጅቶ በመስራትና የሰራዊቱ እንቅስቃሴ ያለ እክል ይካሄድ ዘንድ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃ የማሰባሰብና ለሚመለከተው የሚሊሻ ጽ/ቤት የማስተላለፍ፣ 8. ወንጀል ሲፈጽሙ የተገኙ ግለሰቦችን ይዞ ለፖሊስ አካል ማቅረብ፣ 9. በማንኛውም መንገድ የህብረተሰቡን ፀጥታ የሚያውኩ ሀይሎችን በመከላከል ፀጥታውን አስተማማኝ የማድረግ፣ እና 10.ከበላይ ኃላፊ የሚሰጡ ማንኛውንም ህጋዊ የሆኑ ትእዛዞችን በመቀበል የመፈጸም መታወቂያ የመያዝ ናቸው።[86]

የሚሊሺያ አባላት መብቶች 1. ሠላምና ፀጥታን ለማስከበር የሚሆኑ መሳሪያዎችን ጠይቆ የመታጠቅ፣ 2. ሚሊሻው ፀጥታን የማስከበር ተልእኮውን በመወጣትና ተያዥነት ባላቸው ተግባራት ተሰማርተው እያሉ ከተሰዋና፣ የአካል ጉዳት ቢደርስበት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ያገኛል። (ዝርዝሩ ወደፊት በመመሪያ ይወሰናል።) 3. የተሰጠውን ጉልህ ተግባር እያከናወነ ባለበት ጊዜ ለሚያደርሰው ጉዳት ህጋዊ ተጠያቂነት አይኖረውም። እና 4. እንደአስፈላጊነቱና አቅም በፈቀደ መጠን ህብረተሰቡን በማስተባበር ደንብ ልብስ የማግኘት መብቶች ናቸው።[87] ስምሪትን በተመለከት አዋጁ የሚከተሉትን ያስቀምጣል 1. የሚሊሺያ አባላት ስምሪት ተልእኮውንና አደረጃጀታቸውን መሰረት ያደረገ ሆኖ የጸጥታ ችግር ሲኖር ብቻ የሚፈጸም ይሆናል። 2. ስምሪቱ በሚሊሺያ ሕይወትና ኑሮ ላይ ጉዳትና ምስቅልቅል የሚፈጥር መሆን የለበትም። 3. ማንኛውም ሚሊሻ በሰላም ጊዜ ከምርት ተግባሩ ተፈናቅሎ ስምሪት አይሰጠውም። 4. በዋነኛነት የሚሊሻያው ስምሪት በጎጥና በቀበሌ ክልል ውስጥ ይሆናል፣ እና 5. በአገር ሉኡላዊነት ላይ ችግር ካልገጠመ በስተቀር ማንኛውም የሚሊሺያ አባል ከቀበሌው ክልል ውጪ ስምሪት አይሰጠውም።[88]

ለሚሊሻ የሚሰጠውን ሥልጠና በተመለከተም የአካባቢውን ሠላምና ፀጥታ አስተማማኝ ለማድረግ የሚሊሻውን የህግ ግንዛቤ ብቃት ለማሳደግ ከሚመለከተው የፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት ወሳኝነት ያለው የሚሊሻ አባላት ስልጠና በአጭር ጊዜ የሚሰጥ ሆኖ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ያተኮረ ይሆናል። ሀ. ስለወንጀል መከላከል፣ ለ. ስለኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ሐ. ስለሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች አጠባበቅ መ. ወታደራዊ ትምህርት /በንድፈ ሀሳብና በተግባር / የተደገፈ ሠ. ስለመረጃ አያያዝንና ማስተላለፍን የሚሉ ናቸው።[89]

---

[85] የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የሚሊሺያ አስተዳደርና አደረጃጀት ሥርዓት ደንብ፤ ቁጥር 28/1997 ዓ.ም::

[86] ዝኒ ከማሁ::

[87] የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የሚሊሺያ አስተዳደርና አደረጃጀት ሥርዓት ደንብ፤ ቁጥር 28/1997 ዓ.ም::

[88] ዝኒ ከማሁ::

[89] ዝኒ ከማሁ::

የሰራዊት ግምባታ በአቢዮታዊ ዴሞክራሲ የሚለው መጽሐፍ ከተጠባባቂ ኃይል እና ከብሔራዊ አገልግሎት ይልቅ የሚሊሻ ሥርዓትን የሚያበረታታ የነበር ሲሆን ስለ ሚሊሻ ሥርዓት የሚከተለውን ይላል።

> የሚሊሻ አሰራር አንዳንድ ጠንካራ ጎኖች አሉት፤ የተቀማጭ ኃይሉን ቁጥር አስፈላጊ በሆነ መጠን መወሰን ያስችላል። ወደ ሰራዊቱ የሚቀላቀልን አካል በግለሰብና በሕብረተሰባዊ ክፍል ደረጃ መርጦ እንዲቀላቀል በማድረግ የሰራዊቱን የፖለቲካ ታማኝነትን ለማጎልበት የተሻለ ዕድል የሰጣል። ይህ ኃይል ሰራዊት በማይኖርበት ጊዜ ከዕለታዊ ኑሮው ጋር ደርቦ የአካባቢ ጥበቃ ሥራን እንዲሰራ ማድረግ ይቻላል። ሁል ጊዜ በየአካባቢው የተደራጀ ሆኖ ስለሚገኝ ቀጣይነት ያለው ስልጠና እንዲሰጠው ለማድረግ ወትሮ ዝግጁ መሆኑን ለማረጋገጥና ሞቢላይዝ ለማድረግ የቀለለና የተሻለ ይሆናል። የሚሊሻ አሰራር የራሱ የሆኑ ደካማ ጎኖችም አሉት። ዋነኛው ደካማ ጎኑ ሁል ጊዜ እንደ ግዴታ ሀገሪቱንና ስርዓቱን በመከላከል ተግባር እንዲሳተፍ የማያስገድድና እንዲህ ማድረግ የማያስችል መሆኑ ነው። በተጨማሪም ሰራዊቱ ጥሩ የግንባታ መሣሪያ ሆኖ በተገኘበት ወቅት ከሀገሪቱ የተለያዩ ማዕዘናት የመጡ ወጣቶች በአንድ ላይ ሆነው የሚገነቡበትን ዕድል ለመጠቀም የሚያመች ይሆናል። ሚሊሻው ልክ እንደ እኛ በወጣት አርሶ አደር ላይ የተመሰረተ ከሆነ ከወጣቱ አርሶ አደር የትምህርት ደርጃ ውሱንነት አኳያ የሠራዊቱ መሰረታዊ ተዋጊ የትምህርት ደረጃም ዝቅተኛ ይሆናል። ከሚሊሻው የአሰራር ችግሮች አንዳንዶቹን በሂደት ማቃለል ይቻላል። የወጣት አርሶ አደሩ የትምህርት ደረጃ እያደገ ሲሄድ ሚሊሻ የሚሆነው 8ኛ የደረሰ ብቻ ነው እስከማለት ሊኬድ ይችላል። ይህ ከሆነ ደግሞ ለተቀማጭ ኃይል በቂ የሆነ የአካዳሚ ደረጃ ተይዟል ሊባል ይችላል። ከተለያዩ የሀገሪቱ ማዕዘናት ወጣት ሚሊሻዎችን ሰብስቦ በማሰልጠን ከአሃዶቻቸው ጋር እንዲተዋወቁ አብረው እንዲሰለጥኑ እንዲለማመዱ በማድረግ የሀገሪቱ ወጣቶች እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁና አብረው የሚታነጹበተ የተወሰነ እድል መፍጠርና እንዲኖር ማድረግ ይቻላል። . . . የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብና ልዕልና በሚገባ ባልተረጋገጠበትና የሰራዊቱ የፖለቲካ ግንባታ ዓቅሞች ተፈላጊ በሆነው ደረጃ ላይ ባልደረሰበተ በአሁኑ ወቅት የሚሊሻው ስርዓት የሰራዊቱን የፖለቲካ ጤንነት በማረጋገጥ ረገድ የተሻለ አማራጭ ይሆናል።[90]

ከላይ በተገለፀው የሠራዊት ግንባታ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ በተለምዶ ቀዩ መፅሐፍ ተብሎ በሚጠራው ላይ የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ለማደራጀት ከብሔራዊ አገልግሎት ይልቅ የሚሊሻ ተጠባባቂ ኃይል ተመራጭ መሆኑን ቢያሳይም ከተለያዩ የዓለም አገራት ያለውን የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል አመሰራረት ተሞክሮ ለማየት እንደተሞከረውም በአንድ አገር ውስጥ ዜጎች በእኩልነት አገራቸውን ከተለያዩ ጥቃት የመከላከል፣ የመጠበቅ መብትና ግዴታቸውን የሚገድብ ከመሆኑም በላይ በአርሶ አደር ላይ ብቻ የታጠረ የተጠባባቂ ኃይል መመስረት ዜጎች የአገራቸውን ጉዳይ በንቃት እንዲያውቁ፣ እንዲከታተሉ እንዲሁም አገር አደጋ ላይ ስትወድቅ ከጥቃት የመከላከል አስተሳሰብና ብቃት የሚያቀጭጭ የሚጎዳ ዜጎች በተለይ ወጣቶች ስለአገራቸው ተከፋፍለው የተለያየ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው የመከፋፈል ዝንባሌ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ በአገር ግንባታ ላይ በኢህአዴግ ዘመነ መንግስት የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ በሁሉም ዜጎች ላይ የበላይነቱ አስካልተረጋገጠ ድረስ ሁሉም ዜጎች ለአገራቸው የመቆም ፍላጎትን የሚገድብ መሆኑንና የተጠባባቂ ኃይል ግንባታ በአርሶ አደሩ ላይ ብቻ እንዲሆን ለማድረግ መሞከሩ የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ማደራጃና ማስተባበሪያ ቢሮ የስራ እንቅስቃሴ ላይ የፈጠረው ችግርንም አብሮ በማየት የፈጠረው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን ማየት ይቻላል።

## 2.3.3 **አዲሱ የብሔራዊ አገልግሎት**

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ በነሐሴ 2014 ዓ.ም ከወጣቶች ጋር ያደረጉት ውይይት ላይ ስለ ብሔራዊ አገልግሎት አስፈላጊነትን በተመለከት የሚከተለውን ተናግረው ነበር።

> "ወደ ፊት እኛም እያሰብንበት እየተዘጋጀንበት ያለ ጉዳይ ነው፤ አንድ ወጣት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ፣ ወደ ዩኒቨርሲቲ ከመግባቱ በፊት ለጥቂት ወራት የብሔራዊ አገልግሎት አይነት፣ ስያሜው ለጊዜው ያልታወቀ ሰርቪስ ያስፈልገዋል። ያ ሰርቪስ ከክልሉ ውጪ፣ ከአካባቢው ውጪ ያለውን ነገር ለማየት ይጠቀምበታል። እንደከዚህ ቀደሙ አስገዳጅ አናደርግም፣ በግድ ካልዘመትክ አንልም፣ በግድ ሄደህ አገርህን ካላወክ አንልም፣ ነገር ግን አገሩን የማያውቅ ሰው ሥራ አንቀጥርም። ሥራ

[90] "የሠራዊት ግንባታ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ"፤ ገጽ 190፡፡

> የምንቀጥረው ሃይስኩል ጨርሶ፣ ሶስት ወር አራት ወር ወጣ ብሎ አገር ለማየት ለመስራት የሞከረን ሰው፣ ሥራ ስንቀጥር አንዱ መመዘኛችን እሱ ይሆናል። ሁሉም ወጣት ወደ እንደዚህ አይነት ጉዳይ ቢገባ ልናስተናግደውም እንቸገር ይሆናል ከቁጥሩ ብዛት የተነሳ፤ ነገር ግን መጀመር ያስፈልጋል፤ ኢትዮጲያን ሳናቅ ኢትዮጲያን ማልማት፣ ኢትዮጲያን መምራት ስለሚያስቸግር"።[91]

በየካቲት 2015 ዓ.ም በኢፌድሪ የተወካዮች ምክር ቤት በጸደቀው የተሻሻለው የኢፌድሪ መከላከያ ሠራዊት አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 ስለ ብሔራዊ አገልግሎት እንደሚከተለው ተደንግገዋል።

> (ንዑስ አንቀጽ 4) ወታደራዊ ስልጠና ወስደው ለሁለት ዓመታት በሠራዊቱ ብሔራዊ ግልጋሎት ለመስጠት ፍቃደኛ የሆኑ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ወይም የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ አባላትን ተቋሙ ተቀብሎ ግልጋሎት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል። አባላቱ ግልጋሎታቸውን ሲጨርሱ የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል አባላት የሚሆኑ ከሆነ ተቋሙ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተያያዥ መብቶችና ጥቅሞች እንዲጠበቁላቸው ያደርጋል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይገለፃል፤ (ንዑስ አንቀጽ 5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (4) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለተቋሙ ተልዕኮ አስፈላጊ ናቸው ተብለው በሚለዩ ሙያዎች ተቋሙ ፈቃደኛ የሆኑ ሙያተኞችን መልምሎ በብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይልነት ሊይዝ ይችላል።

ይህ ማለት በኢትዮጲያ ታሪክ ከ40 ዓመት በኃላ የብሔራዊ አገልግሎት የሚጀመር ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር የተያያዘውን የተጠባባቂ ኃይልን አስመልክቶ አሁን ያለው መከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት በሁሉም አውዶች ማለትም በምድር፣ በአየር፣ በባህር፣ በሳይበርና በጠፈር/ስፔስ መዋጋት በሚችል መልኩ የተደራጀና አዋጁም "በአውዶቹ መሰረት የሚኖሩ አደረጃጀቶች እንዳስፈላጊነቱ የልዩ ዘመቻዎች ኃይልና ተጠባባቂ ኃይል ሊኖራቸው ይችላል" ስለሚል እጅግ ዘመናዊ የሆነና በምድረ ኃይልና የአርሶ አደሩና የአርብቶ አደሩ የሕብረተሰብ ክፍል ላይ ተሳትፎ የማያደርግበት፣ የተማረውንና የተለያዩ ሞያዎች ባለቤት የሆነውን ዜጋ የሚያሳትፍ እንደሚሆን ይጠበቃል።

በአዲሱ የብሔራዊ አገልግሎት ላይ የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ከወጣቶች ጋር ባደረጉት ውይይት ላይ ከተናገሩት ንግግር መገንዘብ የሚቻለው የሠራዊት ግንባታ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ በሚለው መፅሐፍ ላይ የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል መመስረት ያለበት ከአርሶ አደሩ ብቻ መሆን እንዳለበት የገለፀውንና ሁሉንም ዜጎች የማያሳትፈውን አካሄድ ለመቀየር እንዲሁም ወጣት የአገሪቱ ዜጎች ያለምንም መለያየት አገራቸውን እንዲያውቁና እንዲያገለግሉ የሚያስችል መሆኑን ያመላክታል።

በየካቲት 2015 ዓ.ም በኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፀደቀው የተሸሻለው የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግር ያጠናከረና በአገሪቱ ህግ ተደንግጎ እንዲፀድቅ መደረጉ ሁሉም ዜጎች አገራቸውን የመጠበቅ ፍላጎትና ግዴታ ያጎናፀፈ ነው። ወጣቶች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ ቦኃላ በብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ስር የብሔራዊ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያሰችል ህግ መሆኑ ሁሉም ዜጎች አገራቸውን የመጠበቅ አገሪቱ ጥቃት ሲፈፀምባት ግዳጅ ተቀብሎ ከመከላከያ ሠራዊቱ ጋር የሚሰማራበትን ሁኔታ የሚያመቻች መሆኑን ያመላክታል በተጨማሪ ወጣቶች የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ግንበታ ላይ ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ያስችላል ብሎ ማየት ይቻላል።

የሰራዊት ግምባታ በአቢዮታዊ ዴሞክራሲ የሚለው መጽሐፍ ከታች እንደሚከተለው የብሔራዊ አገልግሎት ድክመቶችን አስቀምጦ ነበር።

> ብዙ ሕዝብ በሚኖርበት ሀገር የተወሰነ ዕድሜ ያለውን ሰው በቀጣይነት ወደ ወታደራዊ ስልጠና በማስገባትና ተራ በተራ በሰራዊቱ እንዲያገለግል ማድረግ ለመከላከያ ከሚያስፈልግ የሰው ኃይል በላይ ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል ማሰልጠንና መያዝን ሊያስከትልና፤ ይህ ደግሞ በአነስተኛ ወጪ የበለጠ የመከላከያ ዓቅም መገንባት የሚለውን መርህ በመሰረቱ የሚያደናቅፍ ሊሆን ይችላል። የሥርዓቱ አስተሳሰብ የበላይነቱን ባላረጋገጠበት ወቅት ሁሉ ዜጋ የሠራዊቱ አባል እንዲሆን ማድረግ የሰራዊቱ ፖለቲካዊ ይዘት ባለማቋረጥ በሚገባውና በሚወጣው ሰው ሊበረዝ ይችላል። ሰው በሰራዊቱ ረጅም ጊዜ

[91] ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) ከወጣቶች ጋር ያደረጉት ውይይት (ክፍል አንድ - ሀ) - YouTube (31:32 – 32:44) https://www.youtube.com/watch?v=5LN6EuVoWKo Accessed on 15 August 2022.

> ስለማይቀይ በሚገባ እንዲገባ ማድረግ የማይቻል ስለሚያደርገውም ችግሩን ትልቅ እንዲሆን የሚያደርገው ይሆናል። . . . ብሄራዊ የውትድርና አገልግሎት አዲስና ካለፈው ተሞክሮ የተነሳ የተጠላ ነገር በመሆኑ ተቀባይነት እንዲኖረውና ለመጠቀሙ የሚጠይቀው ጊዜና ጥረት አነስተኛ አይሆንም።[92]

የብሔራዊ አገልግሎት ላይ የተጠቀሱት ድክመቶች የፖለቲካ አመለካከት ጉዳይ፣ ከሚፈለገው በላይ የሆነ የሰው ኃይል፣ እና አሉታዊ የታሪክ ተሞክሮዎች ሲሆኑ እነዚህ ጉዳዮች አሁን እየተገነባ ያለው የብሔራዊ አገልግሎት አካሄድ ላይ እንቅፋት እንዳይሆኑ ከወዲሁ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው።

## መጠቃለያ

በኢትዮጲያ ዘመናዊና መደበኛ የጦር ሰራዊት ከተመሰረተ በኋላ አራቱም የኢትዮጲያ መንግስታት የዜግነት ውትድርና ሥርአቶችንና ማለትም የተጠባባቂ ኃይል፣ ብሄራዊ ወታደራዊ አገልግሎት እና የሚሊሻ ስርዓትን በተለያዩ መንገዶች፣ በጊዜያቸው ያለውን የጸጥታ ሁኔታ እና የወታደራዊ አስተምህሮአቸውንና የፖለቲካ ርዮተዓለማቸውን መሰረት አድርገው ተግብረውታል።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ብሔራዊ ጦር የመጀመሪያው በዘመናዊ መልክ በሕግ የተደራጀ የተጠባባቂ ኃይል ሥርዓት ሲሆን ወራሪውን የጣሊያን ጦር በሽፍትነት በየቦታው ሲወጋ የነበረውን መሳሪያ ታጣቂ በአንድ እዝ በማምጣት የታለመለትን አላማ አሳክቷል ማለት ይቻላል። በ1966 ዓ.ም የታወጀው የብሔራዊ አገልግሎት ግን በአግባቡ የተደራጀና የታቀደ ቢሆንም ከወረቀት ላይ የዘለለ ወደትግበራ ሳያመራ የንጉሡ ሥርዓት በወታደራዊው መንግሥት ተተካ።

ከ1966 ዓ.ም እስከ 1983 ዓ.ም የነበረው ወታደራዊው መንግሥት እጅግ ግዙፍ የሆነ መደበኛ እና ሕዝባዊ ሠራዊት (የዜጋ ወታደር) በብሔራዊ አገልግሎት፣ በተጠባባቂ እና በሠራተኛ እና የአርሶአደር ሚሊሻ የገነባ ቢሆንም በሥርአቱ የመጀመሪያ አመታት ከተደረጉት የሶማሊያን ወረራ ከመቀልበስና የመሰረተ ትምህርትና መማስፋፋት በሥተቀር የአገሪቱን ሰላምና ደህንነት ከማስጠበቅ አንጻር በረጅም የእርስ በርስ ጦርነት የብዙ ወጣቶችን ሕይወት ከመቅጠፍ በስተቀርና ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል።

አሁን በሥራ ላይ ያለው የተጠባባቂ ኃይል እንደሚፈለገው መጠን አላማውን አሳክቷል ለማለት የማያስደፍርና ከመከላከያ ሰራዊቱ ጋርም ጠንካራ ቁርኝት የሌለው ነው። አብዛኛዎቹም የተጠባባቂ ኃይል አባላት የክልል ሚሊሻን በመቀላቀል በመከላከያ እዝ ወተው በክልሎች የጸጥታ መዋቅር ስር እያገለገሉ ይገኛሉ። የተጠባባቂ ኃይል ማደራጃና ማስተባበሪያ ቢሮም ለመደበኛ ሰራዊት ምልመላን ማካሄድና ለወራሽ ቤተሰቦች የካሳ ክፍያን በማከናወን ሥራ ላይ ተጠምዶ ቆይቷል። ይህም የሆነበት አንዱ ምክንያት "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ" አስተሳሰብ የሚሊሻ ሥርዓትን እንጂ የተጠባባቂን ኃይልን የማያበረታታ መሆኑ በዋናነት ይጠቀሳል። ነገር ግን በቅርቡ በሥራ ላይ የዋለው የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ጠንካራ የሆነ የዜግነት ውትድርናን በብሔራዊ አገልግሎትና ተጠባባቂ ኃይል ግንባታን ያለመ ሲሆን ይህም ሁሉም ኢትዮጲያዊ የሚሳተፍተበትና ያገርን ሉዓላዊነትና ሰላም ማስጠበቅ በአርሶ አደሩ ጫንቃ ላይ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዜጎች መሆኑን የሚያመላክት ነው። በመሆኑም የተሳካ የዜግነት ሥርዓትን ለመተግበር ካለፉት ስርዓቶች ድክመትና ስኬቶች በመማር አስፈላጊ ነው።

## ዋቢ መጽሐፍት


Adane K Bezabih: The Role of Workers Militia in the Ethio-Somalia War, 1977-78. Munich Personal RePEc Archive, 2022. Online: https://mpra.ub.uni-muenchen.de/115272/

Britannica. Militia. Online: https://www.britannica.com/topic/militia


[92] "የሠራዊት ግንባታ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ"፤ አዲስ አበባ፤ ገጽ 189

Choulis, I., Bakaki, Z., & Böhmelt, T. Public Support for the Armed Forces: The Role of Conscription. Defence and Peace Economics, 1–12. (2019). doi:10.1080/10242694.2019.1709031

Currie, James T. and Richard B. Crossland. "Twice the Citizen: A History of the United States Army Reserve, 1908-1983." Army Reserve, Washington, DC, 1984. Page xiv.

Dawit WoldeGiorgis: *Red Tears: War, Famine and Revolution in Ethiopia.* New Jersey, The Red Sea Press, Inc., 1989.

European Asylum Support Office (EASO) "COUNTRY OF ORIGIN INFORMATION REPORT - ERITREA: NATIONAL SERVICE, EXIT, AND RETURN." 2019. The State Secretariat for Migration, Switzerland. https://coi.euaa.europa.eu/administration/easo/PLib/2019_EASO_COI_Eritrea_National_service_exit_and_return.pdf. Accessed on 08 September 2022.

George T. Kurian: *The Encyclopedia of Political Science.* Washington, DC, CQ Press, 2011.

Guillaume Lasconjarias "Send the Reserve! New Ways to Support NATO through Reserve Forces Contents" Research Paper. Research Division – NATO Defense College, Rome – No. 99 – November 2013. https://www.files.ethz.ch/isn/175315/rp_99.pdf Accesse on 21 May 2022.

Guillaume Lasconjarias "Send the Reserve! New Ways to Support NATO through Reserve Forces Contents" Research Paper. Research Division – NATO Defense College, Rome – No. 99 – November 2013. https://www.files.ethz.ch/isn/175315/rp_99.pdf Accesse on 21 May 2022.

HORN International Institute for Strategic Studies. Open-Ended Conscription in Eritrea's
National Military Service: Here is How to Improve the Policy. HORN POLICY BRIEF. 23 September 16, 2019 https://horninstitute.org/wp-content/uploads/2019/09/OPEN-ENDED-CONSCRIPTION-IN-ERITREA%E2%80%99S-NATIONAL-MILITARY-SERVICE-.pdf. Accessed on 08 September 2022.

Israel Defense Service Law (1986) (jewishvirtuallibrary.org) https://www.jewishvirtuallibrary.org/israel-defense-service-law-1986 Accessed on 22 June 2022

Jukka Mattila et al.: Meanings of Military Ranks, *Defence Studies,* 17:4 (2017) 359-378.

Lars Mjoset – Stephen Van Holde (eds.): *The Comparative Study of Conscription in the Armed Forces.* New Jersey, JAI Press Inc., 2002.

Meller, Bjern: "Conscription and its Alternatives" in Mjoset and Honde (Eds.) (2002.)

National Reserve Forces Committee (NRFC). NATO's ACT. https://www.act.nato.int/nrfc Accessed on 30 May 2022.

Our Soldiers | IDF | IDF (www.idf.il) https://www.idf.il/en/mini-sites/our-soldiers/ Accessed on 22 June 2022

Paulos Milkias: Zemecha: Assessment of the Political and Social Foundations of Mass Education in Ethiopia. *Northeast African Studies*, Spring 1980, Vol. 2, No. 1 (Spring 1980). 19-30.

Provisional Military Administrative Council (PMAC): Declaration of the Provisional Military Government of Ethiopia. Addis Ababa, Berhanena Selam Printing Press, 1974.

Reserve Officers and Reserve Military Officers Law (No. 1076) » TR Laws (av-saimincekas.com) https://www.av-saimincekas.com/en/laws/1076-numbered-reserve-officers-and-substitute-military-officers-law/ Accessed 1 Septmber 2022

Richard Pankhurst "The Ethiopians: A History." Blackwell Publishing, Oxford, 2001. Page 69.

Samuel P. Huntington: The Soldier and the State: the Theory and Politics Civil-Military Relations. Cambridge: The Belknap Press of Harvard University Press, 1967. እና Phil Klay: The Citizen-Soldier: Moral Risk and the Modern Military. Washington, DC, The Brookings Institution, 2016.

Turkey: Law No. 1111 of 1927, Military Law , 20 March 1927, https://www.refworld.org/docid/3ae6b4d020.html Accessed 1 Septmber 2022

Turkey's Constitution of 1982 with Amendments through 2017. https://www.constituteproject.org/constitution/Turkey_2017.pdf?lang=en Accessed on 22 August 2022

Ujházy, László. The Role of Reservists and Reserve Associations today. Security and Defence Quarterly 2018; 19(2)

Unofficial English Translation of the Gazette of Eritrean Laws, 1995-10-23, Vol. 5/1995, No. 11, Page 16. Eritrea - National Service Proclamation No. 82/1995. (ilo.org).

https://www.ilo.org/dyn/natlex/natlex4.detail?p_lang=&p_isn=79562&p_country=ERI&p_count=24 Accessed on 08 September 2022.

William Duane: Military Dictionary. Philadelphia, W. Duane, 1810.

ሌ/ኮሎኔል አበበ ወልደትንሳይ፤ “ቀ.ሠ ና ጦ. ሠ” (ቀዳማቂ ኃይለ ሥላሴ እና ጦር ሠራዊት)፤ አዲስ አበባ፤ 2000 ዓ.ም።

መንግሥቱ ኃይለማርያም፤ ትግላችን የኢትዮጲያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ፤ አዲስ አበባ፤ ፀሐይ አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅት፤ 2004 ዓ.ም።

ራስ ቢት ወደድ - ጀነራል፣ ራስ – ሉታኔት ጀነራል፣ ደጃዝማች – ሜጀር ጀነራል፣ ፊታውራሪ፣ ብርጋዴር ጀነራል፣ ቀኛዝማች – ቀኝአዝማች – ኮሎኔል እና ግራዝማች – ሉታኔት ኮሎኖል ማለት ናቸው። በተጨማሪም ገስጥ ተጫኔ “የቀድሞው ጦር 1927 1983” 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት። ገጽ 17 ላይ ዘርዘር ያሉ የጥንት ማእረጎንች አስቀምጠዋል።

ርስተ ጉልት ወይንም በራስ አገልግሎት የተጐለተ የዘለዐለም ርስት እንዲኾን መንግሥት ፈቅዶለት መሬቱ በርስተ ጉልትነት ተመልምሎ ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ መሬት።

ቃለአብ ታደሠ ሥጋቱ “ሕገ መንግሥት በኢትዮጲያ፡ ከፍትሐ ነገሥት እስከ ኢፌዲሪ” አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር 2011 ዓ.ም።

ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል “ዝክረ ነገር” 1962 ዓ.ም አዲስ አበባ።

ተክለ ጻደቅ መኩሪያ፤ “አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጲያ አንድነት” አዲስ አበባ።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ “የኢትዮጲያ ታሪክ፤ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ” 1936 ዓ.ም።

ኦላና ዞጋ፤ “ግዛትና ግዞት፡ የሜጫ ቱለማ መረዳጃ ማኅበር” አዲስ አበባ፤ 1985 ዓ.ም፤ ገጽ 424።

ከሌ/ኮሎኔል ፍስሃ ደስታ፣ የኢህዲሪ ም/ፕሬዚዳንት ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፤ አዲስ አበባ፤ ሚያዚያ 21 ቀን 2014 ዓ.ም።

ከብ/ጀነራል ውበቱ ፀጋዬ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፤ ግንቦት 26፤ አዲስ አበባ 2014 ዓ.ም።

ክፍሉ ታደሰ፤ ያ ትውልድ የለውጥ ማዕበል በኢትዮጲያ፤ ቅጽ ሁለት፤ አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች፤ 1991 ዓ.ም።

ወታደራዊ ኮሚሳሪያትና የአካባቢ ሕዝባዊ ሠራዊት ማቋቋሚያ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 239/1975 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ።

ዘውዴ ረታ “የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት፡ 1ኛ መጽሐፍ 1923 እስከ 1948 ዓ.ም” አዲስ አበባ፡ ሻማ ቡክስ፣ 2005 ዓ.ም።

የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት እንዲያስጠብቁ እንዲያስጠብቁ ቢመረጡ የቀበሌ አብዮት ጥበቃዎች በዚህ ወቅት የሚታወቁበት ዋናው መለያቸው ግን የደርግ ሥርዓትን የሚቃወሙት ላይ ከፍተኛ የሆነ ግፍ መፈጸም ነበር። ስለ አብዮት ጠባቂዎች የሚከተሉትን መጽሐፍት መመልከት ይቻላል።

የሠራዊት ግንባታ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ፤ አዲስ አበባ።

የብሐራዊ ውትድርና አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 238፤ 1975 ዓ.ም።

የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ማቋቋሚያ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 327/1995 ዓ.ም፤ በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክሲያዊ ሪፐብሊክ።

የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት ቦርዶችን ለማቋቋም የወጣ ትእዛዝ፤ ትእዛዝ ቁጥር 87/1966 ዓ.ም።

የብሔራዊ ወታደርነት አገልግሎት ደንብ፤ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 444/1966 ዓ.ም፤ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 2፤ ጥቅምት 30 ቀን 1966 ዓ.ም።

የብሔራዊ ወታደርነትን አገልግሎት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፤ 1965 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 322።

የንጉሠ ነገሥት ብሔራዊ ጦር ማቋቋሚያ ትእዛዝ ቁጥር 21 1951 ዓ.ም።

የኢፌዲሪ የመከላከያ ሠራዊት ግንባታ ስትራቴጂ፤ የካቲት 2012 ዓ.ም።

የዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ለማድረግ የወጣ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 11/1967 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ።

የእድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ጊዜን ለማራዘም የወጣ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 48/1967 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ።

የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ንብረት ለማድረግ በወጣ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር47/167፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ።

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የሚሊሺያ አስተዳደርና አደረጃጀት ሥርዓት ደንብ፤ ቁጥር 28/1997 ዓ.ም።

የገበሬ ማኅበራትን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 223/1974 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ።

የገበሬዎች ማኅበር ማደራጃና ማጠናከሪያ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 71/1968 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ።

የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣ አዋጅ፤ ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 31/1967 ዓ.ም፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ።

የጦር ኃይሎች ጠቅላይ መምሪያ "የኢፌድሪ መከላከያ ሚኒስቴር የሠራዊት ተልዕኮ" መስከረም 2002 ዓ.ም።

ደጃዝማች ከበደ ተሰማ "የታሪክ ማስታወሻ" አዲስ አበባ አርክቲክ ማተሚያ 1962 ዓ.ም።

ገስጥ ተጫኔ "የቀድሞው ጦር 1927 1983" 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ዜድኤ ማተሚያ ቤት።

ገነነ መሙሪያ፤ ኢህአፓ እና ስፖርት ክፍል 1፤ አዲስ አበባ፤ 2006 ዓ.ም።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) ከወጣቶች ጋር ያደረጉት ውይይት (ክፍል አንድ - ሀ) - YouTube (31፡32 - 32:44) https://www.youtube.com/watch?v=5LN6EuVoWKo Accessed on 15 August 2022.

ፍቅረ ማርቆስ ደስታ "ጃገማ ኬሎ፡ የበጋው መብረቅ (የሕይወት ታሪክ)" አዲስ አበባ፤ ሻማ ቡክስ፤ 2001 ዓ.ም።

ፍቅረሥላሴ ወግደረስ፤ አብዮቱና ትዝታዬ፤ አዲስ አበባ፤ ፀሐይ አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅት፤ 2008 ዓ.ም።